# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 292 ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

# ኢፕድ ባዘጋጀው የአርባ ምንጩ ስለ ኢትዮጵያ መድረክ

- ፌዴራሊዝም ለኢትዮጵያ ልኳም መልኳም መሆኑ ተወስቷል
- ለአንድነትና ለጋራ ማንነት ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ተጠይቋል
- ለሰላም መረጋገጥ መንግሥትና ሕዝብ በጋራና በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ተብሏል

ገጽ 4



ፎቶ-ገበዩ ገብሬ

## «ንጹኃን ዜጎችን ከጠላቶች ሴራ እዳ ከፋይነት ለመታደግ ሁሉም የወንድሙ ጠባቂ መሆን አለበት»

-አቶ ኢብሳ ነጋዎ
የኦነግ ስትራቴጂ አማካሪ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ንጹኃን ዜጎችን ከጠላቶች ሴራ እዳ ከፋይነትና ተጋላጭነት ለመታደግ ሁሉም ዜጋ የወንድሙ ጠባቂ መሆን አለበት ሲሉ የኦነግ ስትራቴጂ አማካሪ አቶ ኢብሳ ነጋዎ ተናገሩ፡፡

አቶ ኢብሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ እየተበራከተ የመጣውን የንጹኃን ዜጎች ጥቃት ለመከላከል ሁሉም የወንድሙ ጋሻና መሆን የግድ ይላል።

«ን ጹኃን ዜጎችን ከጠላቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «በምርምር የሚገኙ ውጤቶች በምክር ቤቱ የለውጥ ማሳለጫ እየሆኑ ነው»

-ዶክተር ምስራቅ መኮንን
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ዋና ጸሐፊ

**ሞገስ ተስፋ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በፓርላሜንታዊ የምርምር ኮንፈረንስ የሚገኙ ውጤቶች በምክር ቤቱ የለውጥ ማሳለጫ እየሆኑ መሆኑን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ዋና ጸሐፊ ገለጹ።ምክር ቤቱ ኃላፊነቱን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ዋና ፀሐፊዋ ዶክተር ምስራቅ መኮንን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዋና ኃላፊነቱ ሕግ ማውጣት፣ አስፈጻሚውን አካል መቆጣጠርና መከታተል፣ ፓርላሜንታዊ ዲፕሎማሲና የሕዝብ ውክልና ሥራን ማከናወን ነው። እነዚህን ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት ደግሞ መረጃና ማስረጃ ያስፈልጋል።

እንደ ዶክተር ምስራቅ ገለጻ፤ መረጃና ማስረጃ ለማግኘት መሰረታዊው ጉዳይ ችግሮችን መለየት፣ ማጥናት፣ ለችግሩ መፍትሔ መስጠት በመሆኑ ይህን ለማድረግ ምርምር ማድረግ ወሳኝ ነው።

የምርምር ሥራው ባለፉት ሁለት ዓመት የተጀመረ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ምስራቅ ፤ ምክር ቤቱ ከዚህ በፊት ከጽሕፈት ቤቱ የሚያገኛቸው ድጋፎችና የምርምር ሃሳቦች ውስን እንደነበሩም ጠቁመዋል።

በዚህ የተነሳ ችግሮችን ከአስፈጻሚው ቀደም ብሎ አውቆ የተመረመሩ መረጃዎችን ይዞ ለመሥራት



ፎቶ-አዩብ ተፈሪ

ይቸግረው ስለነበር ይህን ለማስተካከል፤ የምክር ቤት ጽሕፈት ቤቱ በውስጡ ባለው አደረጃጀት የምርምር ክፍል እንዲኖር ተደርጓል ብለዋል፡፡

ሁሉም መሥሪያ ቤቶች ጥናት የሚያጠኑት በዘርፋቸው ሲሆን፤ ምክር ቤት ውስጥ ግን ወሰን የለውም ያሉት ዶክተር ምስራቅ፤ ሁለንተናዊ ጉዳዮችን በውል መረዳት መተንተንና ማጥናትን ይጠይቃል፤

«በምርምር የሚገኙ ውጤቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ















# የ9 ዓመቱ ታዳጊ ከ100 በላይ መጽሐፍትና አንድ ሺህ ዶላር ለአብርኆት አስረከበ

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ ካሊፎኒያ የሚኖረው የ9 ዓመት ታዳጊ ዳንኤል አዲሱ ከ100 በላይ መጽሐፍት፣ ሁለት ኮምፒውተሮችና አንድ ሺህ ዶላር አሰባስቦ ለአብርኆት ቤተመጽሐፍት አስረከቧል።

የአራተኛ ክፍል ተማሪው ታዳጊ ዳንኤል ለአብርኆት ቤተመጽሐፍት ያበረከታቸው ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ክፍል የተማረባቸውና ከጓደኞቹ ያሰባሰባቸውን የተለያዩ ትምህርታዊና አዝናኝ መጽሐፍት ናቸው።፣ እንዲሁም ሁለት ኮምፒውተሮች በእድሜው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች እንዲጠቀሙበት መስጠቱን ገልጿል።

ሕጻን ዳንኤል መጽሐፍቶቹ ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋን በቀላሉ እንዲማሩ ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑንም ገልጿል።

መጽሐፍቱን ከማሰባሰቡ ባሻገር በርካታ መጽሐፍት ይዞ መምጣት ባለመቻሉ ሁለት ላፕቶፕ ኮምፒውተሮችን እና አንድ ሺህ የአሜሪካን ዶላር የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንዲጠቀሙበት ድጋፍ ማድረጉን ገልጿል።

መጽሐፍቱ ኢትዮጵያውያንን የበለጠ እንደሚደግፉ ተስፋ አለኝ ያለው ሕጻን ዳንኤል፤ በቀጣይም ድጋፍ ማድረጉን እንደሚቀጥል አመልክቷል።

ሁሉም ሕጻናት ጥሩ ትምህርት እና የተሟላ የትምህርት ግብዓት ያስፈልጋቸዋል ያለው ታዳጊው፤ ተማሪዎች ትምህርታቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ስኬታማ እንዲሆኑ መልዕክት አስተላልፏል።

የሕጻን ዳንኤል እናት ወይዘሮ አትጠገብ ግርማ በበኩሏ ልጄ መጽሐፍቱን አሰባስቦ በመምጣቱ ደስተኛ መሆኗን ገልጸዋል።

"ከልጅነቱ ጀምሮ መጽሐፍ ማንበብ ይወዳል፤ ወደ ሀገር ቤት እንደምንመጣ ስነግረው የራሱን የመጽሐፍ መያዣ አዘጋጅቶ መጽሐፍቱን ሰብስቦ ሰጠኝ" ብላለች።

አብርኆት ቤተመጽሐፍት በዚህ ለትውልዱ በሚመች መልኩ መዘጋጀቱን አድንቃ በተመሳሳይ በውጭ የሚኖሩ ተማሪዎች ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርባለች።

በተመሳሳይ ዜናም የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ከአንድ ሺህ በላይ የተለያየ ይዘት ያላቸውን መጽሐፍት ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት አስረከቧል።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ በቀለ፣ መጽሐፍቱን ስናስረክብ ትውልዱን ታሳቢ በማድረግ በመሆኑ ደስታ ይሰማናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ሥራው ሀገር ግንባታ እና ትውልድ ቀረጻ በመሆኑ "ሚሊዮን መጽሐፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ" በሚል መጽሐፍ የማሰባሰቡን ሀገራዊ ጥሪ በመከተል ከመንገድ ምርምር ጋር የተያያዙና ዘርፉን የተመለከቱ መጽሐፍት ማሰባሰባቸውን ጠቁመዋል።

በቀጣይም ጠቃሚ የሆኑና በተለይ ወጣቶች የሚማሩበትና የሚመራመሩበት ከመንገድ ዘርፍ ጋር የተያያዙና ሌሎችንም መጽሐፍት አሰባስቦ ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት ለማስረከብ ቃል ገብተዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማኅበራዊ ጉዳይ አማካሪ ሙዓዘ-ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በርክክቡ ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት ፣መጽሐፍቱ ገበያ ላይ በሚሊዮን ብሮች የማይገኙ በመሆናቸው ለአዲሱ ትውልድ ጠቀሜታቸው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለያየ ሙያ እና በተለያየ ቋንቋ የተጻፉ መጽሐፍትን ገበያ ላይ ማግኘት ቀላል አለመሆኑን ገልጸው፤ በሕክምና፣ በመንገድ፣ በግንባታ፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በሳይንስና በተለያዩ ዘርፎች የተጻፉ መጽሐፍትን በድጋፍ በተገኙ ቁጥር ወደ አብርኆት የሚመጡ ተማሪዎችን ፍላጎት የማርካት እድላቸው ሰፊ መሆኑን ጠቁመዋል።

በመሆኑም የተለያዩ ተቋማት በተለያየ ዘርፍ ላይ ያሉ ልዩ ልዩ መጽሐፍትን እንዲያሰባስቡ እያበረታታን ነው ብለዋል።

በአብርኆት ቤተ-መጽሐፍት በቀን ከሁለት ሺህ እስከ 17 ሺህ በተለይ አብዛኛው ዕድሜያቸው ከ8 እስከ 19 ዓመት የሆኑ ተማሪዎች ከማስጠቀሙ ባሻገር የቱሪስት መዳረሻ ማዕከል እየሆነ መምጣቱንም አመልክተዋል።



ዶክተር አዝመራው አየሁ

# ዩኒቨርሲቲው 77 የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን ማካሄዱን ገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት አመት የማኅበረሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ 77 የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን ማካሄዱን የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ፡

የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የጥናትና ምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር አዝመራው አየሁ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014 በጀት ዓመት ብቻ 77 የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን ማከናወኑንና ከነዚህም ውስጥ 14ቱ ተጠናቀው ወደተግባር እየወረዱ ነው ብለዋል።

ከአምስት ዓመታት በፊት በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ 580 የጥናት ሥራዎች ቢሠሩም አብዛኞቹ የወረቀት ሥራ ብቻ ሆነው መቅረታቸውን የገለጹት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርሲቲው በሀገር አቀፍ ልየታ መሠረት የተግባር ዩኒቨርሲቲ ተብሎ በመመደቡ የሚጠኑ ጥናቶች ሙሉ ለሙሉ ወደ ተግባር ይቀየራሉ ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤በሰሜን ሸዋ ዞን በኢኮኖሚ፣በቱሪዝም፣ በመስኖ ውሃ፣ በኢነርጂ፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በጤና፣ በምግብ ዋስትና በቅርስና በመሰል ዘርፍ ያሉ እድሎችንና ችግሮችን በጥናት መለየት ተችሏል። በቀጣይም ከማኅበረሰቡ ጋር በመሆን ለተለዩ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል።

የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ በማኅበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ የሚሠሩ ፕሮጀክቶች የማኅበረሰቡን ችግር እንዲፈቱ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር አዝመራው፤ የምርምሮቹ መነሻቸውም ሆነ መድረሻቸው ማኅበረሰብ ተኮር ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር አዝመራው ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም በዩኒቨርሲቲው የተሠሩ ምርምሮች ሙሉ ለሙሉ ማኅበረሰቡን ጠቅመዋል ባይባልም በተወሰነ ደረጃ የጠቀሙ ፕሮጀክቶች ነበሩ። አሁን ላይ የሚሠሩ ጥናቶችና የማኅበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ያሉባቸውን ችግሮች የሚቀርፉ እንዲሆኑ በማሰብ እየሠራ ነው። የአካባቢውን ሴክተር መሥሪያ ቤትና የአካባቢውን ጸጋ ባማከለ መልኩ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የኅብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የትኩረት መስኮች ተለይተው ወደ ሥራ ተገብቷል።

ዩኒቨርሲቲው ባሉት አራት የምርምር ማዕከሎች ምርምሮችን እያካሄደ ነው ያሉት ዶክተሩ፤ በተለይ የሀገር በቀል እውቀትን በጥናት በመደገፍ ወደ ማኅበረሰቡ እንዲወርዱ እየተደረገ ነው ብለዋል። በቀጣይ ዩኒቨርሲቲው የማኅበረሰቡን ችግር በሚቀርፍ መልኩ በፍጥነትና በተከታታይነት ሥራዎችን እንደሚሠራና መጭው ትውልድ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ማነጽ አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎችን በተግባር የተደገፈ ትምህርት ለመስጠት እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ዩኒቨርሲቲዎች ትውልድን የመቅረጽ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ሀገርን የመምራት ኃላፊነት አለባቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ከሀገር አልፈው እንደ ስማቸው ዓለም አቀፍ ችግርን በመለየት መፍትሔ ማፍለቅ እንዳለባቸው ጠቅሰዋል።

ሀገራዊ ችግሮች የዩኒቨርሲቲ ችግሮች መሆናቸው በመገንዘብ ዩኒቨርሲቲዎች በጥናቶቻቸው መፍትሔ ፈላጊ መሆን አለባቸው ያሉት ም/ፕሬዚዳንቱ፤ ሀገርን ማሻገር የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ በመንቀሳቀስ ሀገር በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ የተሻለች እንድትሆን መሥራት ይጠበቃል ብለዋል።

# ሕገ ወጥነትን ለመከላከል የከተማዋ ነዋሪ ከደንብ አስከባሪዎች ጋር በቅርበት መሥራት እንደሚኖርበት ተገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የሚስተዋለውን ሕገወጥነትን ለመከላከል የከተማዋ ነዋሪ ከደንብ አስከባሪዎች ጋር በቅርበት መሥራት እንደሚኖርበት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ገለጸ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ኮሚሽነር ፍስሐ ጋረደው የአስተዳደሩ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን አመራሮችና ሠራተኞች ‹‹የደንብ ጥሰትን እንከላከላለን ደማችንን ለወገናችን እንለግሳለን›› በሚል መሪ ቃል ትናንት ደም ሲለግሱ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ በማኅበረሰብ መካከል የሕግ ጥሰትና ወንጀል የሚፈጽሙ አካላት በቁጥር ጥቂቶች ናቸው።ተግባራቸው የብዙኃኑ ጥቅም ተጻራሪ ስለሆነ ሕዝቡም ከደንብ አስከባሪዎች ጋር በቅርበት በመሥራት ሕገወጥነትን ለመከላል የሚደረገውን ጥረት መደገፍ አለበት።

የደንብ ማስከበር ኦፊሰሮችም የደንብ መተላለፍ ተግባራትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በሐቀኝነትና በቅንነት መሥራት እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

ባለስልጣኑ የደንብ ጥሰት በቀጥታ ከዜጎች ኑሮ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የደንብ መተላለፎችን እየተቆጣጠረ የሕዝቡን ጥቅም ለማስጠበቅ እየሠራ መሆኑን አመልክተው፤ ባለስልጣኑ በሚሰጠው የደንብ ማስከበር አገልግሎት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማቃለል የድርሻውን እየተወጣ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የባለስልጣኑ ሠራተኞች ሕግን ከማስከበር ባለፈ በማኅበረሰቡ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማቃለል የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ፣ የችግኝ ተከላ በማከናወንና በሌሎችም የልማት ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በትናንትናው ዕለትም የወገናቸውን ሕይወት ለመታደግ የደም ልገሳ ማድረጋቸው የሚያስመሰግናቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋሁን አሉላ በበኩላቸው፤ ባለስልጣኑ በከተማው ውስጥ የሚስተዋሉ የደንብ ጥሰቶችን የመከላከል፣ የመቆጣጠርና እርምጃ የመውሰድ ሥራዎችን ይሠራል ።በተጨማሪም ኅብረተሰቡ በደንብ ጥሰት ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው የግንዛቤ ፈጠራ ተግባራትን እንደሚከናውን አስረድተዋል።

የደንብ መከላከል ኦፊሰሮችና ሠራተኞች ከሕዝብ የወጡ እንደመሆናቸው ከመደበኛ ሥራዎች ጎን ለጎን የተለያዩ በጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ እየሳተፉ መሆኑን ጠቁመው፤ ደም መለገስ፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስና አረንጓዴ አሻራ ላይ መሳተፍ ከሚከናወኑ የበጎ አድራጎት ሥራዎች መካከል መሆናቸውን ገልጸዋል።

በትናንትናው ዕለት የተከናወነው የበጎ ፍቃድ ደም ልገሳ የማስጀመሪያ መርሐግብር ነው ያሉት ጽሕፈት ቤት ኃላፊው፤ በቀጣይነትም በክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች የበጎ ፍቃድ ደም ልገሳው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

የባለስልጣኑ ደንብ ማስከበር ኦፊሰሮች ሁሌም የሚተጉት ሰላም እንዲሰፍንና ኅብረተሰቡ በሰላም እንዲኖር ስለሆነ ሕዝቡም ተገቢውን ትብብር ሊያደርግላቸው ይገባል ብለዋል።

በደም ልገሳ መርሐ ግበሩ ላይ ከሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች የተውጣጡ ከአንድ ሺ በላይ አመራሮች፣ የደንብ ማስከበር ኦፊሰሮችና ሌሎችም የባለስልጣኑ ሠራተኞች ተሳትፈዋል።

# የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሰላም ግንባታ ተግተው እንዲሠሩ ጥሪ ቀረበ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሰላም ግንባታና የብሔራዊ ምክክር ሂደቱ አካታችና ግልጽነት የተሞላበት እንዲሆን ተግተው እንዲሠሩ ጥሪ ቀረበ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣንና የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ምክር ቤት ሳምንት "ንቁ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሰላም፣ለዲሞክራሲና ለልማት" በሚል መሪ ቃል ከሰኔ 23 እስከ ሰኔ 25 በተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚከበር ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣንና የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ምክር ቤት ሁለተኛው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚከበርበትን ሳምንትን የተደረገውን ቅድመ ዝግጅት አስመልክቶ በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጂማ ዲልቦ በዚሁ ወቅት እንዳስታወቁት፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከመንግሥትና ከግሉ ዘርፍ ጋር በጋራ የጀመሩትን መልካም ግንኙነት አጠናክረው ይቀጥላሉ።በምክንያታዊነት የሚያምን መብትና ግዴታውን በውል የተረዳ፣ የነቃና በነጻነት የተደራጀ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የተጀመሩ የልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሥራዎች ሊጠናከሩ ይገባል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሳምንት ሲከበር ዋና ዓላማው የዘርፉን የገጽታ ግንባታ ማሳደግና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብርን ማጠናከር ነው ያሉት አቶ ጂማ፤ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሰላም ግንባታ ጥረት መትጋት አለባቸው ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከዚህ በፊት በነበረው ጎታች ሥርዓት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዳልተወጡ ገልጸው፤ አሁን አዋጁ የተሻሻለ በመሆኑ ከነበረባቸው ድባቴ ወጥተው መሥራት አለባቸው።በተለይም መጪው የብሔራዊ ምክክር ሂደት አካታችና ግልጸኝነት የተላበሰ እንዲሆን በቅርበት ማገዝ ይገባቸዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሄኖክ መለሰ በበኩላቸው እንደገለጹት፣

የሲቪል ማኅበረሰብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ዜና

# «የጥፋት ኃይሎች ክፉ ድርጊት ሳያስቆመን በአረንጓዴ አሻራ የአንድነት መሠረት እያኖርን ነው»

-ከንቲባ አዳነች አቤቤ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡-የጥፋት ኃይሎች ክፉ ድርጊት፣ ተፈጥሯዊም ሆነ የፖለቲካ ልዩነት ሳያስቆመን በአረንጓዴ አሻራ ለትውልድ የሚሻገር የአንድነት መሠረት እያኖርን ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

ከንቲባዋ 4ኛው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በአዲስ አበባ ከተማ ትላንት ይፋ ሲሆን በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው እንደገለጹት፤ መብላት ካላቆምን በስተቀር ችግር ገጠመን ብለን መሥራት ማቆም አንችልም። የጥፋት ኃይሎች ክፉ ድርጊት፣ ተፈጥሯዊም ሆነ የፖለቲካ ልዩነት ሳያስቆመን በአረንጓዴ አሻራ ለትውልድ የሚሻገር የአንድነት መሠረት እያኖርን ነው።

የነገ የታሪክ ፍኖት በዛሬ ምዕራፍ ላይ የተመሠረተ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ያልዘራነውን ልናጭድ ወደማሳው አንዘልቅም፤ መሬታችንን ሳናለሰልስ ዘራችንን አንበትንም፤ ዛሬን በትጋት መሥራት ሳንችል ቀርተን ነገ ብሩህ ቀን ይሆን ዘንድ በምኞት ማዕበል ለመናጥ አንፈቅድም። ለሥራ እንጣደፋለን፤ ለውጤቱም እንተጋለን ሲሉ ገልጸዋል።

የዛሬው አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብራችን የግዙፉ ትልም አንዱ አካል መሆኑን አመልክተው፤ መሬት እንንካ፤ ከራሳችን እንጀምር፤ ኢትዮጵያ ለሁላችንም ትበቃናለች፤ አካባቢያችንን እናልማ፤ ከተማችንን እናስውብ፤ ችግኝ እንትከል ብለዋል።

ትልቁን የብልጽግና ራዕያችንን በጋራ እውን ለማድረግ ከሚያወራ የሚሠራ፤ ከሚያማ የሚያለማ ፤ ከሚገፋ የሚያቅፍ፤ ከሚጠላ የሚወድ ከሚገድል የሚያድን ትውልድን የመገንባት አንዱ አካል መሆኑንም ጠቅሰዋል።

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ አገኘው ተሻገር፣ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኤርጎጌ ተስፋዬ



የአዲስ አበባ ብልፅግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ መለሰ ዓለሙ፣ እንዲሁም የፌደራል እና የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና አርበኞች ጥሪ የተደረገላቸው የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት አራተኛው ዙር የአረጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በአዲስ አበባ ከተማ በይፋ ተጀምሯል።

በ4ኛው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በአዲስ አበባ በሁሉም ክፍለ ከተሞች 11 ሚሊዮን የተለያዩ ችግኞች መዘጋጀታቸው በመርሐ ግብሩ ላይ ተገልጿል። የአዲስ አበባን የአየር ሁኔታ ለማሻሻልና ለዜጎችም የምትመች ከተማ ለማድረግም የአረንጓዴ አሻራን ማኖር ይገባል ተብሏል።

የተለያዩ ሀገር በቀል እፅዋትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኞች የሚተከሉ ሲሆን፥ በአጠቃላይ 40 በመቶ ችግኞች የውበት፣ 40 በመቶ የጥላ እንዲሁም 20 በመቶ ደግሞ ምግብ ነክ ናቸው።

የዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በሀገር አቀፍ ደረጃ ባለፈው ሳምንት መጀመሩ ይታወሳል።

# ሚኒስቴሩ 20 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየሠራ ነው

•ስደተኞችን የሚደግፍ አዲስ ፕሮጀክት ይፋ ሆኗል

በዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የሥራ አጥነት ክፍተትን በመዳሰስ እስከ 2030 ድረስ 20 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለመፍጠር ማቀዱን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ። ኤ.ኢ.ሲ ኢትዮጵያ ስደተኞች ራሳቸውን ችለው የአገር ኢኮኖሚን ከፍ ለማድረግ የሚያስችል አዲስ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሥራ፣ ስምሪትና የገበያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን፤ የሥራ አጥነት መጠን ስምንት ነጥብ ስምንት በመቶ መድረሱን እና በየዓመቱም ሁለት ሚሊዮን ተመራቂ ወጣቶች ገበያውን እንደሚቀላቀሉ ተናግረዋል።

በሥራ አጥነት ላይ ያለውን ክፍተት በመዳሰስ እስከ 2030 ድረስ 20 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለመፍጠር መታቀዱንም አመልክተዋል። ይህ እውን የሚሆነው የግል ዘርፉ፣ የልማት አጋሮች እና መንግሥት የጋራ ተሳትፎና ጥረት ሲታከልበት መሆኑንም አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ ስደተኞችን የምትቀበልበት ፖሊሲ ክፍት መሆኑን በመጠቀምም፤ በሀገር ውስጥ ካሉ ተፈናቃዮች በተጨማሪ ከ800ሺ በላይ ተፈናቃዮችን ተቀብላ እያስተናገደች እንደምትገኝም ጠቁመዋል። ስደተኞች ዕዳ ሳይሆኑ ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት እና ለቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ እንዳላቸው እንደሚታመንም ነው የተናገሩት።

ኤ.ኢ.ሲ ኢትዮጵያ በሚል ይፋ የሆነው ፕሮጀክትም በሥራ ዕድል ፈጠራ ችግሮችን ለመቅረፍ ጉልህ ሚና እንደሚኖረውም ተናግረዋል።

በሀገር ውስጥ በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ ምክንያቶች ለተፈናቀሉ ወገኖች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፤ ከሳዑዲ የሚመለሱ ኢትዮጵያውያንም ወደ ሥራ ለማሠማራት ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ እንደሚገኝም ነው የጠቆሙት።

የኤ.ኢ.ሲ ሥራ አስኪያጅ አቶ ንዋይ አለማየሁ በበኩላቸው፤ ይፋ የሆነው አዲሱ ፕሮጀክት ስደተኞች ራሳቸውን ችለው የሀገር ኢኮኖሚን ከፍ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።



በተመረጡ የአፍሪካ ሀገራት የሚገኙ ስደተኞችና ወጣቶች ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ የሚሠራው ኤ.ኢ.ሲ ኢትዮጵያ በየአካባቢዎቹ የሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ ሥራ ፈጣሪዎችን በመደገፍ የሀገርን ኢኮኖሚ ከፍ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ነው የገለጹት።

ኤ.ኢ.ሲ ኬንያና ሩዋንዳን ጨምሮ በተመረጡ ስምንት የአፍሪካ ሀገራት ላይ የሚሠራ ድርጅት ሲሆን፤ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በሥራ ፈጠራ ላይ ትኩረት በማድረግ በአሶሳና በጂግጂጋ 250 ሺ ለሚደርሱ ጥቃቅንና አነስተኛ ሥራ ፈጣሪዎችን አቅም ለመፍጠር እንደሚሠራ ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ በአሶሳና በጂግጂጋ ከ600 በላይ ጥቃቅን እና አነስተኞችን ድጋፍ እየሰጠ እንደሚገኝም ተናግረዋል። ድርጅቱ ከስደትና ስደት ተመላሾች ኤጀንሲና ከዳሽን ባንክ ጋር የመግባቢያ ስምምነት መፈጸሙን እና ከመሰል ተቋማትና ተራድኦ ድርጅቶች ጋር እንደሚሠራም ተናግረዋል። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ብቻ 100 ሺህ ሥራ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ ዕቅድ መያዙንም ነው የተናገሩት።

የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ /ዩኤን.ኤች.ሲአር/ የኢትዮጵያ ተወካይ ራኦል ክርስቶፎር ኒት በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ከ800 ሺህ በላይ ስደተኞችን ተቀብላ ማስተናገዷ የሚመሰገንና የስደተኞች የመሥራት መብት መጠበቁ ሊበረታታ የሚገባው መሆኑን ጠቁመዋል።

ስደተኞች ብዙ ጊዜ ከኢኮኖሚ ተሳትፎ እንደሚገለሉ አስታውሰው፤ ሥራ ፈጠራው ከልማት አጋር እና ከግል የልማት ዘርፉ ጋር በመተባበር የሚተገበር መሆኑን ተናግረዋል። የተመድ የስደተኞች ኤጀንሲ /ዩኤን.ኤች.ሲአር/ ስደተኞች ራሳቸውን ችለው ሀገርን እንዲጠቅሙ ማስቻል ዓላማው ያደረገ መሆኑንም ተናግረዋል።



ኮሎኔል ጌትነት አዳነ

# የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሱዳን ምርኮኞችን ገድሏል በሚል የሚነዛው መረጃ መሠረተ ቢስ መሆኑ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የምርኮኞችን አያያዝ ባልጠበቀ መንገድ ወታደሮቹን ገድሏል በሚል የሱዳን ጦር የሚነዛው መረጃ መሠረተ ቢስ መሆኑን የኢፌዴሪ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ገለጸ።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በቦታው እንዳልነበርና የኢትዮጵያን ግዛት ዘልቆ የገባው የሱዳን ኃይል ከአካባቢው ሚሊሻዎች ጋር መጋጨቱንም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ኮሎኔል ጌትነት አዳነ በሰጡት መግለጫ፤ አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት በፈፀመበት ወቅት የሱዳን ሠራዊት የኢትዮጵያና የሱዳን ሕዝብ ታሪካዊ ወዳጅነትን በማይመጥን መልኩ በኢትዮጵያ ግዛት ላይ ወረራ መፈጸሙን ጠቅሰዋል።

የሱዳን መከላከያ ኃይል በተለያየ ጊዜ ውስጣዊ ችግሮች ባጋጠሙ ቁጥር በኢትዮጵያ ላይ ትንኮሳዎችን ሲያደርግ መቆየቱንም ነው ያነሱት።

ከሰሞኑም የሱዳን ኃይል ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ዘልቆ በመግባት በአካባቢው በነበሩ የኢትዮጵያ ሚሊሻዎች ላይ ጥቃት ማድረሱንና ከሁለቱም ወገን ጉዳት መድረሱን ተናግረዋል።

ይህም ሆኖ እያለ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በስፍራው ባልነበረበት ሁኔታ ምርኮኞችን ገደለ በሚል የሱዳን ጦር ክስ ማቅረቡ ተቀባይነት የሌለውና መሠረተ ቢስ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በቦታው አልነበረም ያሉት ኮሎኔል ጌትነት፤ ምርኮኞችን ቢይዝ እንኳን ሕግ አክባሪነት፣ ሕዝባዊነትና ግዳጅ አፈፃፀም የሠራዊቱ መለያ ባህርያት ናቸው ነው ያሉት።

የሠራዊቱ ዲሲፕሊን በኮሪያና በኮንጎ ዘመቻዎች ጭምር የተመሰከረለት መሆኑን ጠቅሰው፤ በሁለቱ ሱዳኖች የአብዬ ግዛት እንኳን በስነ ምግባሩ እንደተወደሰም አንስተዋል።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ከመንግሥት ትዕዛዝ ሳይሰጠው እንደ ሽፍታ የሚንቀሳቀስ ቡድን ሳይሆን በጥብቅ የዕዝ ሰንሰለት የሚመራ እንደሆነም ኮሎኔል ጌትነት ተናግረዋል።

የደረሰውን ጥቃት በተመለከተ ማጣራት የሚፈልግ አካል ካለ ከሁለቱ ሀገራት መከላከያ ሠራዊት ተወካዮች የተውጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ እንዲጣራ ለመተባበር የኢትዮጵያ ሠራዊት ዝግጁ መሆኑንም አረጋግጠዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# ኢፕድ ባዘጋጀው የአርባ ምንጩ ስለ ኢትዮጵያ መድረክ

- ፌዴራሊዝም ለኢትዮጵያ ልኳም መልኳም መሆኑ ተወስቷል
- ለአንድነትና ለጋራ ማንነት ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ተጠይቋል
- ለሰላም መረጋገጥ መንግሥትና ሕዝብ በጋራና በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ተብሏል

**ፍቃዱ ከተማ**

ርጥብ ሳር ይዘውና ተንበርክከው በቀልን በይቅርታ፤ ቁጣን በትዕግስት በሚቀይሩ የጋሞ አባቶች ምድርና የፈጣሪ የውበት ጥበብ በተፈጥሮ ፍንትው ብሎ በሚታይበት አርባ ምንጭ ከተማ ላይ ታድመናል። የአርባምንጩ ፓራዳይዝ ሎጅ ከወትሮው ለየት ባለ መልኩ ትናንት ገና ከረፋዱ በተለያዩ አልባሳት ባሸበረቁ እናቶች፣ አርሶና አርብቶ አደሮች፣ በጋሞ አባቶች እንዲሁም በምሑራንና ፖለቲከኞች ደመቅመቅ ብሎም ይታያል።

ከዋናው መንገድ ፊት ለፊት በኮብል ድንጋይ በተሰራው ጌጠኛ መንገድ ግራና ቀኝም የታላቋን ሀገር ኢትዮጵያን የረጅም ዘመን ታሪክ የሚናገሩ፣ ያለፈችበትን የፖለቲካ ውጣ ውረድ የሚያሳዩና አሸባሪው ሕወሓት በሀገራችንና በሕዝቦቿ ላይ ያደረሰውን ግፍና ለዚሁ የተከፈለውን አኩሪ መስዋዕትነት ብሎም የተገኙ ድሎችንና በለውጡ ዘመን በፈተና ውስጥ ለስኬት የበቁ ሜጋ ፕሮጀክቶችን የሚያመላክቱ ፎቶግራፎች በሥነ ሥርዓትና የተመልካችን ቀለብ በሚይዝ መልኩ ተሰድረዋል። ከዚህ ስፍራ ትንሽ ከፍ ብሎ በስተቀኝ የሚገኘው ትልቅ አዳራሽም የጥበበኞች አዕምሮ ተጨንቆበትና ተጠቦበት የመድረኩን ዓላማ በሚመጥን መልኩ ውብና ማራኪ ሆኖ ተወያዮችን ይጠብቃል።

የዚህ ሁሉ ውብ ዝግጅት መነሻና መድረሻ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት "ስለኢትዮጵያ" በሚል መሪ ቃል ሰላም፣ ዴሞክራሲና እውነተኛ ፌዴራሊዝም በሚል ርዕስ ያሰናዳው የፎቶግራፍ አውደርዕይና የምክክር መድረክ መከናወን ነው። ከጅግጅጋ፣ ከድሬዳዋ ሐረርና ሃዋሳ ከተሞች በመቀጠል ለአምስተኛ ጊዜ አርባ ምንጭ ከተማ ላይ የተካሄደው ይህ ሁነት በይፋ የተጀመረው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር በአቶ ርስቱ ይርዳው፣ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ እናቶች፣ አርሶና አርብቶ አደሮች የፎቶግራፍ አውደ ርዕዩ ተመርቆ ለዕይታ ክፍት በማድረግ ነው። በዚህም በርካቶች የኢትዮጵያን ያለፈ ታሪክ መለስ ብለው ቃኝተውበታል፤ በሚኮራው ኮርተውም በሚያሳዝነውም በእንባ ጭምር ኀዘናቸውን ገልጸዋል።

ከዚህ ሁነት በመቀጠል ትኩረቱን በኢትዮጵያ ሰላም፣ ዴሞክራሲና እውነተኛ ፌዴራሊዝም ግንባታ ላይ ያደረገው ውይይት መድረክ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልልዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳው መሪነት የተካሄደ ሲሆን በመድረኩ ሶስት ጽሑፍ አቅራቢዎች ለመነሻ የሚሆን ሀሳብ አቅርበዋል። በመድረኩ መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ እንደተናገሩት፤ ኢፕድ በኢትዮጵያ ጉዳይ ሁሉም ሰው ይመለከተዋል፤ ሊነጋገርም ይገባዋል በሚል ዕሳቤ በአስራ ሁለት ከተሞች ላይ ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች በሚል መርሕ ትኩረታቸውን በተለያዩ ታላላቅ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያደረጉ መድረኮችን ለማካሄድ አቅዶ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል።አምስተኛውን መድረክም አርባምንጭ ላይ ለኢትዮጵያ ሰላምና ልማት ጉልህ ድርሻ ያላቸውን እናቶች፣ አርሶና አርብቶ አደሮች እንዲሁም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በማሳተፍ እያካሄደ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የመጀመሪያው የጽሑፍ አቅራቢ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ማዕከል ሚኒስትር ዶክተር አብዲ ዋሳ ሲሆኑ ሰላምና ዴሞክራሲ በሚል ርዕስ ባቀረቡት የመነሻ ሃሳብ ሰላም ለሁሉም ነገር መሠረት መሆኑን፣ ለሰላም መስፈን ኢትዮጵያውያን የበርካታ እሴቶች ባለቤት መሆናቸውን፣ ከቤተሰብ እስከ ሃገር ሰላም እንዲሰፍን በመቻቻል በይቅርታና በመከባበር ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንደሚገባው አብራርተዋል። ዴሞክራሲና ሰላም ተመጋጋቢ ናቸው ያሉት ዶክተር አብዲ ፤ ለዴሞክራሲ መስፈን የተቋማት ግንባታና ባህል ወሳኝ መሆናቸውን ተናግረዋል። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ ጥሩ ጅምሮች እንዳሉና ሊጠናከሩ እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተዋል።

ሁለተኛው ጽሑፍ አቅራቢ የኢፌዴሪ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተርና ታዋቂው ፖለቲከኛ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ እውነተኛ ፌዴራሊዝም በሚል ርዕስ ባቀረቡት የውይይት መነሻ ሃሳብ የፌዴራሊዝም ሥርዓት ለኢትዮጵያ ነባራዊ ችግሮች ሁነኛ መፍትሔ መሆኑን አውስተው፤ ይሁንና በሕወሓት ዘመን በኢትዮጵያ የተተገበረው ፌዴራሊዝምና የመደብለ ሥርዓት ፖለቲካ በሸፍጥ የተሞላ፤ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ግለሰቦች ለአፈናና ግድያ የዳረገ በመሆኑ የከሸፈው ገና ከጠዋቱ መሆኑን አብራርተዋል። ሕወሓት የግጭትና የሴራ ፖለቲካ የሚከተል ኃይል በመሆኑም ለእውነተኛ ፌዴራሊዝምና ዴሞክራሲ የሚሆን ባህሪ በፍጹም እንደሌለውም ተናግረዋል።

ሰላም ለኢትዮጵያ ቀዳሚና ወሳኝ ጉዳይ ነው ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ በኢትዮጵያ አሁን ላለው የሰላም መታጣት ከውስጥ እኔ ካልመራሁ ሀገር መፍረስ አለባት ብሎ የተነሳው ወያኔ፤ ከውጭ ደግሞ የኢትዮጵያ ታላቅነትና ገናናነት ዕረፍት የነሳቸው አንዳንድ ሀገራት መሆናቸውን ጠቁመዋል። ስለሆነም እነዚህን በሕግ ማስከበርና በዲፕሎማሲ መፍሔሄ ሊሰጣቸው ይገባል ብለዋል።

የቋንቋ፣ የባህል የሃይማኖትና የአስተሳሰብ ብዝኃነት ላላት ኢትዮጵያ የፌዴራሊዝም ሥርዓት ተመራጭ ነው ያሉት ደግሞ ሦስተኛ ጽሁፍ አቅራቢው የኢፌዴሪ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ማዕከል ሚኒስትር ዶክተር ቢቂላ ሁሪሳ ናቸው። ዶክተር ቢቂላ በገለጻቸው ምንም እንኳን ሥርዓቱ ተመራጭ ቢሆንም ባለፉት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ የተተገበረበት መንገድ የብሔር ማንነትና ልዩነት ላይ አተኩሮና አንድነትን ዘንግቶ በመሆኑ በሀገራችን አሁን እየተፈጠሩ ላሉ ችግሮች መንስኤ ሆኗል ይላሉ።

በክልሎች ላይ ሲደረግ የነበረውም ጣልቃ ገብነት የከፋና በሀገራቸው ጉዳይ እኩል ተሳታፊ የመሆን መብት የነበራቸውን ሕዝቦች ያገለለ በመሆኑ እውነተኛ የፌዴራሊዝም ሥርዓት አልነበረም ሲሉ አብራርተዋል። ስለሆነም በለውጡ ዘመን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብትን ባከበረ ነገር ግን ኢትዮጵዊነትንና የጋራ ማንነትን በሚያጎላ መልኩ እውነተኛ የፌዴራሊዝም ሥርዓት ሁለንም ዜጋ ባሳተፈ መልኩ በመተግበር ላይ መሆኑን አውስተዋል።

በውይይቱ መጨረሻ ሀሳባቸውን ያቀረቡት የመድሩኩ መሪ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳው መወያየትና መነጋገር እጅግ አስፈላጊ በሆነበት በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በዚህ ወሳኝ ርዕስ ይህን የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የውይይት መድረክ በማሰናዳቱ ትልቅ ምስጋና ይገባዋል ብለዋል።ሰላም፣ ዴሞክራሲና እውነተኛ ፌዴራሊዝም ለኢትጵያ ብልጽግናና ለሕዝቦቿ ደኅንነት ወሳኝ ጉዳዮች መሆናቸውን አስምረውበታል።

እውነተኛ የፌዴራሊዝም ሥርዓት ለኢትዮጵያ አዋጪ መሆኑ በውይይቱ ታምኖበታል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በአተገባበር ሂደት የታዩ ግድፈቶች ሊታረሙና አንድነትንና የጋራ ማንነትን በሚያጎላ መልኩ መተግበሩ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ አሁን በተለያዩ ቦታዎች እየታየ ያለው የሰላም መደፍረስና የጭካኔ ተግባራት የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች በመቀናጀት የሚያስፈጽሙትና ዋነኛ ዓላማውም ሀገር ማፍረስና የህዳሴ ግድብን ማደናቀፍ መሆኑን አብራርተዋል። ስለሆነም ኢትዮጵያውያን ይህንን ጠንቅቀን ማወቅና በሀሰት መረጃዎች ሳንፈታ የጠላቶቻንን ሴራ ማክሸፍ አለብን ሲሉ ሃሳባቸውን ደምደመዋል።

## «ንጹኃን ዜጎችን ከጠላቶች ሴራ እዳ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጥቃቱ በሚሰነዘርባቸው አካባቢዎች ሕዝቡ አቅሙ በፈቀደ መጠን አሸባሪዎቹን ካልተከላከለና አሳልፎ ለሕግ ካልሰጠ ችግሩ በጸጥታ አካላት ብቻ የሚቃለል አይሆንም ያሉት አቶ ኢብሳ፤ ድርጅታቸው ሰሞኑን በተለይ በግምቢ በቶሌ አካባቢ በንጹኃን ላይ የተወሰደ አስነዋሪ ጥቃት ለማውገዝ ብሎም መሰል ጥቃቶች እንዳይፈጸሙ ሕዝቡ አሸባሪዎችን አምርሮ በመታገል ወንድሙን እንዲታደግ ባወጣው መግለጫው ጠይቋል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ኢብሳ ማብራሪያ፣አነግ በአገሪቱም ሆነ በዓለም ነባራዊ ሁኔታ የትጥቅ ትግል አዋጭ አለመሆኑን በመገንዘብ ሠራዊቱን ጭምር ወደ ሀገር የመለሰ የፖለቲካ ድርጅት ቢሆንም ከሰላማዊ ትግሉ ያፈነገጡ ሶስት በመቶ የማይሞሉ አካላት ጫካ ቀርተው ችግር እየፈጠሩ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ሕግ ከማስከበር ጋር ተያይዘው ከቡድኑ ጋር በሚደረገው ፍልሚያ ባለፉት ሦስት ወይም አራት ዓመታት ከማንም በላይ ትልቅ መስዋዕት የከፈለው የኦሮሞ ሕዝብ መሆኑ መታወቅ አለበት ያሉት አቶ ኢብሳ፤ ሆኖም አንዳንድ ወገኖች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሕዝቡ ወንድሙንም ሆነ እራሱን ለመታደግ የሚከፍለውን መስዋዕት ወደ ጎን በመተው ሕዝብን እንደሕዝብ የመፈረጅና ጥረቱንም ዋጋ ለማሳጣት የሚያደርጉት ጥረት መታረም አለበት ብለዋል፡፡

በትጥቅ ትግሉ ወቅት ቶሌ የኦነግ ሠራዊት በስፋት ሲንቀሳቀስ ከነበረው አካባቢ አንዱ በመሆኑ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በደንብ እንደሚያውቁ የተናገሩት አቶ ኢብሳ፤በተለይ በረሃብ ምክንያት ከወሎ ወደ አካባቢው የመጡ ሕዝቦች ራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ የኦሮሞ ሕዝብ ቤት በመሥራት፣ በሬ በመስጠት በአጠቃላይ ያለውን በማካፈል እንዳቋቋማቸውና የኦነግ ሠራዊትም ቢሆን አንድም ቀን ሕዝቡን በክፉ ዓይን ሳያይ እንደ ኦሮሞ ሕዝብ ሲንከባከባቸው መቆየቱን አውስተዋል፡፡

ዳሩ ግን ጠላቶች በተለይ ሁለቱ ሕዝቦች ኦሮሞና አማራ አንድ እንዳይሆኑ ለዘመናት በሰሩት ሴራ በሕዝቦቹ ጥርጣሬ እንዲነግስ ማድረጋቸውን ያስገነዘቡት አማካሪው፤ እንደሚደለቅ የጥፋት ከበሮ የሚፈጠረው ችግር ከቁጥጥር ውጪ የሚሆን ቢሆንም ሕዝቦቹ ቀድሞውንም በደም የተሳሰሩ በመሆናቸው እስከዛሬ ድረስ አንድነታቸውን ማስቀጠል መቻላቸውን መስክረዋል።

እውነታው ግን የኦሮሞ ሕዝብም ሆነ የኦነግ ሠራዊት በሌላው ላይ ጥቃት አድራሽ ቢሆን ኦሮሚያ ውስጥ በሰላም የሚኖሩ ሁሉም ብሔሮች መኖር አይችሉም ነበር ያሉት አቶ ኢብሳ፤ አንድ ወቅት ሕወሓት በመቀሌ በመሰብሰብ በተለይ አቶ መለስ ዜናዊ "ለሕወሓት የሚያበቃው ኦሮሞና አማራ አንድ ሲሆኑ ነው" ካሉ በኋላ ውሎ ሳያድር በወቅቱ እራሳቸው የሚያደርጉትና የሚቀርጹት ድራማ "ኦነግ በአርባ ጉጉና በደንገጎ አማራዎችን ጨፈጨፈ" በሚል የሠሩት ሴራ መቼም አይረሳም ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የኦሮ-ማራ ጥምረት ያስደነገጠው አቶ ጌታቸው ረዳ "እሳትና ጭድ እንዴት ሊስማሙ ቻሉ? በመሠረቱ ይህ የሕወሓት ድክመት ማሳያ ነው" ማለቱ የሕዝቦች ጥምረት ሕወሓትን ምን ያህል እንደሚያሳስብ መታወቅ አለበት ያሉት አቶ ኢብሳ፤ ከዚህ አንጻር አገር እያሸበሩ ያሉ ጽንፈኞችና አክራሪዎች በየአካባቢው እንደ አሸን እንዲፈሉ ከማድረግ አኳያ የሕወሓት ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ሕዝቡ የጠላቶቹን ሴራ ለማክሸፍ በመከራ ውስጥ እንኳ አንድነቱን ማጠናከር እንዳለበት ጠይቀዋል።

ከዚህ በኋላ በጠላቶች ሴራ በየትኛውም አካል በንጹኃን ላይ የሚፈጸም ግፍ መቆም አለበት ያሉት አማካሪው፤ አስፈላጊ ከሆነ የጸጥታ ችግር ያለበት አካባቢ ለጊዜው በጸጥታ አካላት እንዲተዳደር ያስፈልጋል ብለዋል።

## «በምርምር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይህን ለማድረግ የምርምር ጥናት ማዕከል በማቋቋም ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር ለመሥራት የሚያስችል አሠራር ተዘርግቶ ሥራ መጀመሩን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ምስራቅ ገለጻ፤ ዩኒቨርሲቲዎች በራሳቸው ተመራማሪዎችና አዳዲስ ግኝት ፈላጊዎች በመሆናቸው ያደረጓቸውን የምርምር ውጤቶችና በምክር ቤቱ ውስጥ ያሉትን አጀንዳዎች ለዩኒቨርሲቲዎች ቢሰጡ ምርምሩን ስለሚያጎለብቱ ምክር ቤቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የትብብር ስምምነት አድርጎ እየሠራ ነው፡፡

የምርምር ኮንፈረንሱ በምክር ቤቱ የሚደረጉ የምርምር ውጤቶችን የለውጥ ማሳላጫ አድርጓቸዋል ያሉት ዋና ጸሐፊዋ፤ በተደረጉ ምርምሮች ቋሚ ኮሚቴ ሲደራጅ፣ አሰራሮች ሲሻሻሉ፣ የምክር ቤቱ የስነ ምግባር ደንብ እንዲሻሻል የሚያደርጉ ሃሳቦች ላይ ተመስርቶ ነው ብለዋል፡፡

እስካሁን ባለው ሂደት የምክር ቤቱም ሆነ የፌዴራል መንግሥቱ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት ባለው መልኩ እንዲመራ ዝርዝር ማንዋል እንዲዘጋጅ ተደርጓል ያሉት ዶክተር ምስራቅ፤ምርምሩ ጠቃሚ ሃሳቦች የተገኙበት መሆኑንም አስታውሰዋል።

እንደ ዶክተር ምስራቅ ገለጻ፤ በእያንዳንዱ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ምክር ቤቱ ሚና አለው። በምክር ቤቱ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሕዝብን ድምጽ የሚያሰማ ክርክር ለማድረግ ጥናትና ምርምሮች አጋዥ ናቸው።

ምክር ቤቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ኃላፊነት የሚሰማው ምክር ቤት እየሆነ ነው ያሉት ዶክተር ምስራቅ፤ ለአብነትም በዚህ አመት የጤና ኢንሹራንስ አዋጅ ቀርቦ ነበር፣ በአዋጁ ላይ ሁሉም የምክር ቤት አባላት ከወከሉት ሕዝብ ጋር በመወያየት ሃሳብ ይዘው በመምጣት በምክር ቤቱ ተጨምቆ የሕግ አካል መሆን የሚችለው ወደ ሕግ አካል እንዲገባ የተደረገበት ሂደት አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል።አስፈጻሚው ሥራውን በትክክል እንዲሠራ በማድረግ ሂደት ውስጥም ለውጦች መኖራቸውን ዶክተር ምስራቅ መኮንን ተናግረዋል።

## የሲቪል ማኅበረሰብ...

ከ2ኛው ገጽ የዞረ

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሳምንት ሲከበር ከመንግሥት ከመገናኛ ብዙኃን፣ ከግሉ ዘርፍ ጋር ያላቸውንና የሚኖራቸውን ግንኙነት ከቀድሞው የበለጠ ለማሳደግ ነው።በተጨማሪም በጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ በአንድነት ለመሥራት ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነው።

እንደ አቶ ሄኖክ ገለጻ፤ በሳምንቱ በሚዘጋጀው መድረክ ላይ የሰብዓዊ ዕርዳታ ስርጭት በአገር በቀል ድርጅቶች እንዲከናወን የማድረግ እንቅስቃሴ፤ አዲሱ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 1113/2011 ከወጣ በኋላ ያለው የሲቪል ማኅበራት ተሳትፎ፤ ፈተናዎችና መልካም አጋጣሚዎች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶ በሰላም ግንባታ ሚና ምን እንደሚመስል ይቀርባል።በተጨማሪም ሥርዓተ ጾታ በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ በሚሉ ጉዳዮች ላይ የፓናል ውይይትና የሀሳብ ልውውጥ ይደረጋል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሄኖክ ማብራሪያ፤ ሁለተኛው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሳምንት ለማክበር ሲታቀድ በዘርፉ ያሉ ድርጅቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚደረገው ማናቸውም እንቅስቃሴ ያላቸውን ሚና ለሕዝብና ለባለድርሻ አካላት እንዲያስተዋውቁ ዕድሉን ለመፍጠር ነው።

ሁለተኛው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች "ንቁ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሰላም፣ ለዲሞክራሲና ለልማት" በሚል ሀሳብ ከሰኔ 23 እስከ ሰኔ 25 ቀን 2014 ዓ.ም እንደሚከበር ተገልጿል። በአሁኑ ወቅት ከሶስት ሺ 700 በላይ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በምክር ቤቱ ተመዝግበው እንደሚገኙም ታውቋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስግዳጅ ሁሌም ዝግጁ የሆነ ሰራዊት እንዳለን ስአፍታም መዘንጋት ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፍላል!

የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ከፍ ባለ ህዝባዊነት፣ አገር ወዳድነትና ዲሲፕሊን የተገነባ ሰራዊት ነው። አሁነኛ ወታደራዊ ቁመናው እና ዝግጁነቱ በየትኛውም ጊዜና አስቸጋሪ ሁኔታ የሚሰጠውን ግዳጅ የመፈጸም አቅም የተላበሰ ነው። በዚህም የመላው ህዝባችን አስተማማኝ ሀይል ከሆነ ውሎ አድሯል።

በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የመከላከያ ሀይሉን ስትራቴጂክ በሆነ መልኩ ከማዘመን ጀምሮ አቅሙን ለማሳደግ የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ ሁለንተናዊ ስራዎች የተሰጠውን አገርና ህዝብን የመጠበቅ ኃላፊነት በተሻለ መልኩ መታደግ የሚያስችለውን አቅም እየፈጠሩለት ይገኛሉ።

መቼምና በየትኛውም ዘመን አገሩን ለጠላት ፍላጎት አሳልፎ ከመስጠት የክብር ሞት ከሚመርጠው የኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የወጣው የአገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት፤ በየዘመኑ አገር ችግር ውስጥ መሆኑዋን ተከትለው ጦር ሰብቀው የሚወጡ፤ ለአገር ስጋት የሚሆኑ ሃይሎችን በታላቅ ተጋድሎ ድል የመንሳት ታሪክ ባለቤት ነው።

በሌሎች ላይ ጦር የመስበቅ /የጠብ አጫሪነት /ታሪክ የሌለው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት፤ ከጠባጫሪነት ይልቅ በሰላም አስከባሪነት በተለያዩ አገራት በመሰለፍ ህዝባዊነቱንና ሰላም ወዳድነቱን በተጨባጭ ያስመሰከረና እያስመሰከለረ ያለ የሰላም ሀዋሪያ የሆነ ሰራዊት ነው።

ሰራዊቱ ግጭት የቱንም ያህል ለአንድ ህዝብ፤ በተለይም ለድሀ ህዝብ ተግዳሮት እንደሆነ ከራሱ የታሪክ ተሞክሮ የሚረዳ፤ የየትኛውም አገር ህዝብ ከግጭት ያተርፋል ብሎ የማያምን፤ ከዚህም የተነሳ ግጭት ቀስቃሽ የሆኑ አጋጣሚዎችና ክስተቶችን በልዩ ሁኔታ ተረድቶ ማለፍ የሚያስችል የዳበረ አቅም ባለቤት ነው፡፡

ይህ የዳበረ አቅም በቀደሙት ዘመናት በሰላም ማስከበር አለም አቀፍ የግዳጅ ቀጠናዎች በተጨባጭ ማሳየት የቻለ፤ በዚህም አለም አቀፍ እውቅና የተቸረው ሰራዊት ነው። ይህን ባህሪውን ሰራዊቱ ውስጥ በተካሄዱና እየተካሄዱ ባሉ የሪፎርም ስራዎች ከፍ ወደ አለ የስብእና ደረጃ እንዲያድግ እየተሰራ ነው።

ይህ በሆነበት ሁኔታ ከትናንት በስቲያ የሱዳን የመከላከያ ሚኒስትር ይህን ሰራዊት በመወንጀል ያወጣው መግለጫ ከተጨባጭ እውነታነት ይልቅ የፖለቲካ ይዘት ያለውና የጠብ አጫሪነት መንፈስ የተሞላ ነው። እንደተለመደው የአገር ውስጥ የፖለቲካ ጫናን የማስተንፈሻ መንገድ ፍለጋ አካል ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ቀደም ባለው ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ መንግስት “ጎረቤት የክፉ ቀን ደራሽ ነው “በሚል አሸባሪው ሕወሓት ትግራይ በነበረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት በሰነዘረበትና አገርን ችግር ውስጥ በጣለበት ወቅት ለጥበቃ አደራ የተሰጠውን መሬት ወስዶ እስከ ዛሬ ፋከራ ላይ እንዳለ ይታወቃል።

መላው አለምና ህዝባችን እንደሚታወቀው መንግስት ከሁሉም በላይ በሁለቱ አገራት ህዝቦች መካከል ያለው ግንኙነት ከሚመጡና ከሚሄዱ መንግስታት ፍላጎት በላይ መሆኑን ተገንዝቦ፤ ችግሩን ከሀይል ይልቅ በሰላማዊ ድርድር ለመፍታት ውሳኔ ላይ ደርሶ ነገሮችን በትዕግስት እየተከታተለ ይገኛል።

የመሬት ይገባኛል ጥያቄዎችን በኃይል ለመፍታት የሚደረግ ሙከራ ከፖለቲካ ቁማርነት ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። በታሪክ ውስጥም አገራትና ህዝቦችን ደም ከማፋሰስ ውጪ ዘላቂ መፍትሄ ሆኖ አያውቅም። እንደኛ ላሉ በድህነት አረንቋ ውስጥ ለሚገኙ ህዝቦች ደግሞ ችግሩ የቱን ያህል ዋጋ የሚያስከፍል ሊሆን እንደሚችል መገመትም አይከብድም።

የሱዳን የሽግግር መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ አንድም የሌሎች ኃይሎች አጀንዳ ተሸካሚ በመሆን፤ ከዚያም ባለፈ በአገር ውስጥ እያጋጠሙት ያለውን የተቃውሞ አቅጣጫ ለማስቀየር ከማንም በላይ ለሱዳን ህዝብ ወንድም እና የክፉ ቀን ደራሽ በሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ግልጽ የሆኑ የጠላትነት ተግባራትን በአደባባይ በመፈጸም ላይ ይገኛል።

ዛሬም ቢሆን፤ ሰኔ በገባ ማግስት ግርግሮችን በመፍጠር የድንበር አካባቢዎችን የግጭት ወረዳ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት፤ በሁለቱ አገራት ግጭት የመቆመሪያ ካርድ እናገኛለን ብለው ከሚያስቡ የሱዳንና የውጪ ኃይሎችና ቡድኖች የተሳሳተ ስሌት የመነጨ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ለእነዚህ ቡድኖችና ኃይሎች የመቆመሪያ ካርድ አይሆኑም።

እንደቀደመው ጊዜ ውሉ በሁለቱ አገራት ህዝቦች መካከል ያለውን ዘመን የተሻገረ ጉርብትናና ከዚህ የሚመነጨውን ወንድማማችነት ታሳቢ በማድረግ ችግሮች እስከ መጨረሻው በሰላም እንዲፈቱ ይጥራል። ከዚህ ያለፈ የህዝብና የአገርን ሉአላዊነት የሚደፍር ሁኔታ ካጋጠመ ግን እንደ አገር መቼና የትም ግዳጅን በአስተማማኝ ሁኔታ መወጣት የሚችል ለዚህም ሁሌም ዝግጁ የሆነ ሰራዊት ባለቤት መሆናችንን ለአፍታም መዘንጋት አይገባም። ይህን መዘንጋት ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፍላል።


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ህግ የማስከበር ዘመቻውን በማጠናከር ስጋት ውስጥ ያሉ ዜጎችን መታደግ !

**በእምነት**

ኢትዮጵያዊ አብሮ መኖሩ፣ አንተ ትብስ አንተ ብሎ ተቻችሎ፣ አንዱ ላንዱ ክንዱ እንጂ ደመኛው ሳይሆን፤ በቤተሰብ መካከል አልያም በጎረቤት ችግር ሲፈጠር አንተም ተው አንተ ተው ተባብሎ በሽማግሌ ሰላም የሚያወርድ፤ የተፈጠረውን ችግር ሁሉ ረስቶ እንደቀድሞ ለመሆን የሚችል ቅን ልብ ያለው ህዝብ ነው።

ልጆቹን እንኳን ሳይሰስት ለእህት ለወንድሙ ከዛም ራቅ ብሎ ላመነበት እንዳንተ እንዳንቺ አድርገሽ አሳድጊ ይጠቅምሻል፤ ትጠቅምሻለች ብሎ ለመስጠት የማይሳሳ ለየት ያለ የመተሳሰብ ባህል ባለቤት ነው ።ይህ ከፍቅር የሚመነጭ አብሮነት ለብዙ ዓመታት አብረን እንድንኖር ዓለም እንደ ብርቅ እንዲያየን ስለ እኛ እንዲያስብና እንዲመራመር ያስገደደ ሃቅ ነው።

ዛሬ ይህ ሁሉ አደጋ ውስጥ ገብቶ ለእኛም ለአለምም ግር በሚያሰኝ ችግር ውስጥ ወድቀን እንገኛለን ፤ ወንድም በወንድሙ ላይ እየጨከነ ያለበት መንገድ ከሰው ልክ የሚያወጣን እየሆነ ነው። ለምን በአግባቡ ልንጠይቀውና ምላሽ ልንሰጠው የተገባ ጉዳይ ነው ።

የትናንት ታሪካችን ሩህ ሩህ ልብ ያለን፣ ካለቀሰ ጋር አብረን የምናለቅስ፣ ሳይኖረን የምናካፍል፣ ለእኛ ይቅርብን ብለን የሌሎችን ችግር ለመድፈን የማንሳሳ ነበር። ይህ ወርቃማ እሴታችን የት ሄደ?

ምናልባት መሰልጠን መሰይጠን ሆኖብን ይሆን? በወንድም እህቶቻችን ላይ እንድንነሳ ያደረገን? ወይስ እምነቱም ባህሉም ሁሉንም ጣልነውና የተጫነብንን የስግብግብነትና የራስ ወዳድነት መንፈስ ተግተን በአደባባይ ሰከርን? ያለንበት ሁኔታ፤ እየሄድንበት ያለው መንገድ ሁሉም ግራ የሚያጋባ፤ ከእኛ ኢትዮጵያውያን ፍጹም የማይጠበቅ ለማመን የሚያስቸግር ሆኗል።

በእርግጥ አሻባሪው ሕወሓት ባለፉት 30 ዓመታት የጫኑብን የዘር ፖለቲካ ለዚህ እንዳበቃን ለመናገር የሚከብድ አይደለም፤ ስለምን ግን ይህንን መርዝ በዚህ ደረጃ ተጋትነው? ቡድኑ በቀደደልን እኩይ መንገድስ ለምን በዚህ ደረጃ ፈሰስን? ።

እንደ እኔ አንድ ሰው አገሩ የተወለደበት ሳይሆን ያደገበት ፣ንብረት ያፈራበት፣ ቤተሰብ መስርቶ ወግ ማዕረግ ያየበት ነው።የእኛ የኢትዮጵያውያን ኑሮም እንደዛው ነው። ሰሜን የተወለደ ምናልባት እድገቱና ኑሮው ቤተሰቡን የሚመሰርተው ወይም የመሰረተው ደቡብ ሊሆን ይችላል።ይህ ሰው ታዲያ በዘሩ ምክንያት ችግር ደረሰበት ተብሎ ሲነገር መስማትን ያህል ከባድ ዜና ከወዴት ይገኛል።

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ናት እያልን ደጋግመን እንናገራለን፤ አዎ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ናት፤ ያውም ሁሉም የየራሳቸው መገለጫ ያላቸው ባህላቸው፣እንግዳ አቀባበላቸው፣ ጋብቻ ስርዓታቸው፣ የችግር አፈታት ዘዴያቸው (ሽምግልናቸው) ኸረ ስንቱ ሁሉም የየራሱ ውብ ባህልን የያዘ ነው።

ከዚህ ውስጥ ደግሞ ለእኔ ኦሮሞና ባህሉ እጅግ ይለይብኛል ።ሰው አክባሪነት፣ ልምላሜ ወዳድነት፣የልጅ ፍቅር፣ እንኳን የወለደውን ሰው የወለደውን ተቀብሎ ከልጁ በላይ አሳድጎ ወግ ማዕረግ የሚያደርስ፤ ተካፍሎ አካፍሎ መብላትን የሚያውቅ፣ በገዳ ስርዓት የራሱን ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መስርቶ ለአገር ተምሳሌት በሆነ መልኩ የሚኖር ድንቅ ህዝብ ነው።ዛሬ ግን እያየን ያለነው ነገር እውነት የኦሮሞ እናት ማህጸን ያፈራቻቸው ሰዎች ናቸው፤ አገርን በዚህ ልክ ማቅ እያለበሱ ያሉት ያስብላል።

በገዳ ሥርዓት መሰረት ወንድም ወንድሙን መግደል አጸያፊ በመሆኑ ወንድሙን የገደለ ሰው ከጎሳው ተለይቶ ሰባት ወንዝ ተሻግሮ እንዲኖር እንደሚደረግ አባ ገዳዎች ይናገራሉ፡፡ታዲያ ዛሬ ወንድም እህቶቻቸውን ህጻናትን ሳይቀር በግፍ በማያውቁት ነገር እየገደሉ ያሉት የሰው አውሪዎች ላይ ምን ዓይነት ፍርድ ነው የምንጠብቀው? እንኳ ማሰብ ራሱ ይከብዳል።

በኦሮሞ ባህል እርስ በእርስ መታኮስ ከገዳ እሴቶች ጋር የሚጣረስም እንደሆነ ነው አባገዳዎቹ የሚናገሩት፡፡ በስርዓቱ መሰረት የማስታረቅ ስራዎች ካልተሰሩ በስተቀር ገዳይ ወደ ኅብረተሰቡ እንደማይቀላቀልም ይነገራል ።በኦሮሞ ስም የሚታገል ሁሉ ለገዳ ሥርዓት እሴቶች በመገዛት ራሱን ከዚህ አይነት አፀያፊ ድርጊት ሊያርቅ እንደሚገባም ነው አባገዳዎች የሚናገሩት፤ ታዲያ እነዚህ አውሬዎች ወንድሞቻቸውን እየገደሉ ስለ ምን ሊያወሩ ይችላሉ?

ይህ የክፋት ተግባር በእኛ መካከል መፈጠሩ ያሳዝናል ግን ደግሞ ተፈጥሯል ምንም ማድረግ አይቻልም፤ አሳሳቢው ጉዳይ ግን ከዚህስ በኋላ ሞትን እየተለማመድን መኖር ወይንስ እነዚህን ሰው በላ ቡድኖች አጥፍቶ ሁሉም በአገሩ የትም ሆኖ መኖር እንዲችል ማድረግ? ይህ ሊመለስ የሚገባው ወሳኝ ጥያቄ ይመስለኛል።

አሁን ባለው ሁኔታ ኅብረተሰቡ በሠላም እጦት እየተቸገረ ነው፤ ሠላም ለማስፈን ሁሉም በመነጋገር ለሠላም እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በማስወገድ መፍትሄ ማስቀመጥ የግድ ነው። ኅብረተሰቡም ሠላም እንዲመጣ የበኩሉን ሁሉ ሊወጣ ይገባል። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ወጋችን ነው።ለተፈጸሙ ሰብዓዊ ጥቃቶች ፍትህ መስጠት፣ መሰል ጥቃቶችም እንዳይደገሙ ጥንቃቄ ማድረግ ከመንግስት የሚጠበቅ ለነገ ይደር የማይባል ጉዳይ ነው።

አባቶቻችን ለአያሌ ዓመታት በሰላም አብረው በመኖር አገር እንዳስረከቡን ከታሪክ ተምረናል፣ እኛም ወግ ደርሶን ለማየት ችለናል፤ አሁን ላይ ግን የተለየየ ታረጋ የለጠፉ ግለሰቦች የፖለቲካ ትርፍ ፍለጋ ምንም በማያውቁ ንጹኃን ዜጎች ደም እየቆመሩ፤ በዚህም ብዙ ዋጋ እያስከፈሉን ነው።

ዜጎች በማንነታቸው ብቻ የነዚህ ቆማሪዎች ሰለባ እየሆኑ ነው። በአገሪቱ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይሆን ተለዋዋጭ ባህሪ በመያዝ በሁሉም አካባቢ እየደረሱ ነው።ይህንን ሰንኮፍ ከላያችን ላይ ነቅሎ መጣል ለአንድ አካል ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ ነው።

የጠላቶቻችን ዓላማ ስስ ብላታችንን በማጥናት በተለይ በማንነት እንድንጨራረስና እንድንበተን ተግተው መስራት ነው፤ ከዚህ አንጻር ሰሞኑን የሆነው ነገር በቂ ማሳያ ነው። የጥቃቱ አድማስ ብቻ ሳይሆን አሳቃቂነቱም ከፍ ብሏል።

ይህን ሁኔታ ፈጥኖ መቆጣጠር ያስፈልጋል። “ሳይቃጠል በቅጠል” እንደሚባለው ችግሩን በማያዳግም ሁኔታ ለማስወገድ መንግስት የጀመረውን ሕግ የማስከበር ዘመቻ በተጠናከረና በተናበበ መልኩ ሊያስቀጥለው ይገባል። በዘመቻው የሚገኘውን ውጤትም በየጊዜው ለህዝብ ማስታወቅ ይጠበቅበታል ።እስካሁን ለጠፋው የሰው ሕይወት ፍትህ ለናፈቀው ህዝብ ፍትህን ማረጋገጥ ቀጣይ አጀንዳ ሊሆንም ይገባል።

የወቅቱ ዋነኛ ስራ መሆን ያለበት የተጀመረውን ሕግ የማስከበር ዘመቻ በማጠናከር ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ያሉ ዜጎችን መታደግ ነው። መላው ህዝብ በተለይም ጥቃት በሚካሄድባቸው አካባቢ የሚገኙ ዜጎች ዘመቻውን ባላቸው አቅም ሁሉ መደገፍ ይኖርባቸዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ


# ‹‹በልጆቼ አባትና በወረዳ አመራሮች ሴራ ከሶስት ልጆቼ ጋር ጎዳና ተጥያለሁ››

- አቤቱታ አቅራቢዋ ወይዘሮ ሰላማዊት ሃብታሙ

ሙሉቀን ታደገ

**የዛሬው « የፍረዱኝ « አምድ ዝግጅታችን በአዲስ አበባ ከተማ ፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ልዩ ስሙ ታይዋን ሰፈረ ሰላም እየተባለ ወደ ሚጠራው አካባቢ ይወስደናል:: የዛሬዋ አቤቱታ አቅራቢ ወይዘሮ ሰላማዊት ሃብታሙ ትባላለች::**

**« የቀድሞ ባለቤቴ እና የሁለት ልጆቼ አባት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ከወረዳ አራት አስተዳደር እና ከቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ለበርካታ ዓመታት ከኖርኩበት እና ልጆቼንም ወልጄ ካሳደኩበት የቀበሌ ቤት በግፍ በማስወጣት ሦስት ልጆች ይዤ ጎዳና እንድወድቅ አድርገውኛል » ስትል አቤቱታዋ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እንዲወጣላት ሕዝብና መንግሥት እንዲፈርዳት ጠይቃናለች። በዚሁ መሰረትም አቤቱታዋን ከአንደበቷ አድምጠን ፣ ሰነዶችንም መርምረንና አቤቱታ የቀረበባቸውን አካላት ጭምር አነጋግረን ለዛሬ ያዘጋጀነውን እነሆ ለንባብ ብለናል።**


አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 4 ወሳኝ ኩነት
ምዝገባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
Addise ketema Sub-City worda 4 vital event registration

ቁጥር ________
ቀን ________

ለ ________

አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የወረዳው ነዋሪ መሆናቸውን ይመለከታል::

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ነባር ቀበሌ ___ በቤት ቁጥር ___ ውስጥ ነዋሪ የሆኑት አቶ/ወ/ሮ//ወ/ሪት ________ የወረዳው ነዋሪ መሆናቸውን ጠቅሰን እንድናፍላቸው በ___/___/2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀውናል ::

በዚህ መሰረት አመልካች አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ________ ከላይ ቁጥሩ በተገለፀው ቤት ውስጥ የቀበሌው ነዋሪ መሆናቸውን ከወረዳው ካለው ማህደር /ቅጽ/ ያረጋገጥን መሆኑን እየገለጽን የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግላቸው ስንል በትህትና እንጠይቃለን::

ከሰላምታ ጋር

Addis Ketema Sub-City
Administration
Vital Event

### የትዳር አጋር

አቤቱታ አቅራቢዋ ወይዘሮ ሰላማዊት እንደገለጸችው፤ እድገቷ እና ኑሮዋ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 በተለምዶ ታይዋን ሰፈረ ሰላም ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። የእህል ውሃ ነገር ሆነና በ2002 ዓ.ም እዚያው ባደገችበት ሰፈር አቶ እሸቱ አበራ የተባለውን ውሃ አጣጪን አገኘች። ውሃ አጣጪን ያገኘችው ወይዘሮ ሰላማዊት፤ ከጋብቻ በኋላ ቤተሰቦቿን በመተው ወደ ባለቤትዋ ቤተሰቦች በመሄድ አዲስ ቤተሰብ ተቀላቀለች።

ባለቤቷ አቶ እሸቱ ያደገው ባለትዳር ከሆነችው እህቱ ጋር ነው። የአቶ እሸቱ አሳዳጊ እህት እና ባለቤቷ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ቀበሌ 17 የቤት ቁጥር 505 የቀበሌ ቤት ይኖሩ ነበር። የቀበሌው ቤትም በአቶ እሸቱ የእህት ባል በሆነው አቶ ፍቃዱ ክፍሌ ተመዝግቦ ነበር። ከተወሰነ ዓመታት በኋላም በቀበሌ ቤት ይኖሩ የነበሩት የአቶ እሸቱ አሳዳጊዎች የራሳቸውን ቤት ሰርተው የቀበሌ ቤቱን ለአሳደጉት ልጅ ለአቶ እሸቱ እና ለባለቤቱ ወይዘሮ ሰላማዊት ሰጥተው ሄዱ።

እንደ ወይዘሮ ሰላማዊት ገለጻ፤ የትዳርን ሕይወት አንድ ብለው ሲጀምሩ ባለቤቷ በሹፍርና እሷ ደግሞ እንጀራ በመጋገር፣ ልብስ በማጠብ፣ እንዲሁም በእጣ የሚወጣ ጨዋታ በማጫወት ኑሯቸውን አሸንፈው ጥሩ ሕይወት መምራት ይጀምራሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ወይዘሮ ሰላማዊት ከሌላ አባት የምትወልዳትን ልጇን ባለቤቷ ወደ ቤት እንድታመጣት ይጠይቃል። ወይዘሮ ሰላማዊትም ልጅቱ ከአባቷ ጋር እየኖረች ስለሆነ እዚያው ከአባቷ ጋር ብትቀመጥ እንደሚሻል ለባሏ ታስረዳዋለች ። ባልም ምንም ቢሆን እናት እንደምትሻል ይነግራትና ከወይዘሮ ሰላማዊት የመጀመሪያ ባል የምትወለደው ልጅ ወደ እናቷ ቤት እንድትመጣ ይደረጋል።

ቀናት ቀናትን ወለዱ። ወይዘሮ ሰላማዊትም ከትዳር አጋሯ ከአቶ አሸቱ ከሁለተኛ ባለቤቷ ደግሞ የመጀመሪያ የሆነውን ልጅ አረገዘች። ወንድ ልጅም ተወለደ። ይሁን እንጂ ልጁ ከተወለደ በኋላ የባለቤቷ ባህሪ ሙሉ በሙሉ መቀየር መጀመሩን የምትናገረው አቤቱታ አቅራቢዋ ፤ በቤት ውስጥ ሰላም ጠፋ። አለመግባባቱ ከጫፍ ደርሶ ችግሩ ከአቅሟ በላይ ሆኖባት እንደነበር ታስታውሳለች። ይህን ተከትሎ ወይዘሮ ሰላማዊት ነገሩን ለማብረድ በማሰብ ልጆቿን ለባለቤቷ ጥላ ወደ አረብ ሀገር ተሰደደች።

### ጉዞ ወደ አረብ አገር

ልጆቿን ጥላ ወደ አረብ አገር የሄደችበት አንዱና ዋነኛው ምክንያት ከባለቤቷ ጋር የተፈጠረውን ጸብ ለማብረድ ቢሆንም፤ ባለቤቷ አቶ እሸቱ ስለኑሮ ውጣ ውረድ እንዲገባው እና ኃላፊነት እንዲሰማው ለማድረግ አስባ እንጂ ባል እና ሚስት እየሰሩ የሚያገኙት ገቢ የቤታቸውን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት በቂ ሳይሆን ቀርቶ እንዳልነበር ትናገራለች።

ወደ አረብ አገር ከሄደች በኋላ ከባለቤቷ ጋር ትደዋወል ነበር፤ አልፎ አልፎም ገንዘብ ትልክላቸው እንደነበር የምትገልጸው አቤቱታ አቅራቢዋ ፤ ነገር ግን ብዛት ያለው ገንዘብ አንድጊዜም ልካ እንደማታውቅ አልሸሸገችም። ስለሆነም ወደ አገሯ ስትመለስ አረብ አገር የሰራችውን ገንዘብ ብዙም አልባከነም። ከአረብ አገር መልስ ባል እና ሚስት ከስደት በፊት ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት በንግግር ፈተው አብረው መኖር ይጀምራሉ።

### የተሳካ የትዳር ዘመን ቀጠሉ

አገር እንደመጣች ባለቤቷ ሹፌር ስለነበር መኪና ትገዛለታለች። ከመኪናው የሚገኘውን ገንዘብ እንዳያጠፋባት በመስጋት መኪናውን በብድር እንደገዛቸው ትነግረዋለች። ባለቤቷ ሹፍርና ሲሰራ እሷ ደግሞ ጫማ ቤት መስራት ጀምራ ነበር ። ቤታቸውም የሞቀ የደመቀ ሆነ። ትዳራቸውም በሰፈር ሰዎች «ትፍ! ከአይን ያውጣችሁ » ተባለለት። የትዳራቸው መንገዶች ተቃንተው እና ሰምረው ተጨማሪ መኪናዎችንም ገዙ። የስራ ዘርፋቸውንም አስፋፉ። ለስራ የሚያግዛቸውን ረዳት ማፈላለግ ጀመሩ፤ የሚስት እናትም ልጃቸውን በስራ ለማገዝ ከክፍለ አገር መጡ። ሚስትም ለባሏ ሁለተኛ ለራሷ ደግሞ ሶስተኛ ሴት ልጅም ተወለደች።

ይሁን እንጂ ሴት ልጅ መወለዷን ተከትሎ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ባለቤቷ በፊት የነበረው የማይወደድ ጸባዩ ተመለሰ የምትለው አቤቱታ አቅራቢዋ፤ ከባለቤቷ ፀባይ መቀያየር ጋር ታያይዞ ቤቱ ውስጥ ጭቅጭቅ መፈጠሩን ትናገራለች። ባልም ምድር ላይ አሉ የሚባሉ ሱሶችን ይጠቀም ጀመር። ይህን ተከትሎ ኑሯቸው ከማደግ ይልቅ ወደ ኋላ መመለስ ጀመረ፣ መኪኖችም ተሸጡ። ኑሯቸውም በዜሮ ተባዛ፤ ኑሮ ሲበላሽ ባልም ልጆቹን እና ቤቱን ጥሎ እንደጠፋ ትናገራለች ።

ከቤት በጠፋ በሶስተኛው ወር የፋሲካ በዓል አመካኝቶ ወደ ቤት ተመለሰ የምትለው አቤቱታ አቅራቢዋ፤ ከጠፋበት ሲመለስ ቤተሰቡ ደስ ብሎት እንደተቀበሉት ትገልጻለች። ነገር ግን እሱ የበዓል ዕለት ደስታቸውን ለመንጠቅ ረብሻ ፈጠረ። ረብሻውም ተጋግሎ ባል የልጆቹን እናት ከደረጃ ላይ ወርውሮ ይጥላታል። የቤቱ ደረጃም የሚስትን አከርካሪ ክፉኛ በመምታቱ ሚስት ራሷን ሳተች። ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልም ተወሰደች። የጳውሎስ ሆስፒታል አልችልም ስላለ ወደ አቤት ሆስፒታል ሪፈር ይጻፍላታል። በአስራ አምስተኛ ቀኗም ስትነቃ ራሷን ሆስፒታል እንዳገኘችው አቤቱታ አቅራቢዋ ታስታውሳለች።

እንደ አቤቱታ አቅራቢዋ ገለጻ፤ ደረጃው ወገቧን ክፉኛ ስለመታው መላ አካሏ መንቀሳቀስ ያቆማል። ይህን ተከትሎ ባል ተሰወረ። ባልም በፖሊስ ፍለጋ ተይዞ ይታሰራል። በ2011 ዓ.ም ባል እና ሚስት መልሰው ላይገናኙ ፍቺ ፈጸሙ። ፍችውን ተከትሎ ልጆች ከእናታቸው ጋር ቀሩ። በዚህም ባል ለልጆቹ ተቆራጭ እንዲያደርግም ፍርድ ቤት ወሰነ።

ይህን ተከትሎ አቶ እሸቱ የቀበሌ ቤቱ የእርሱ መሆኑን ገልጾ ከቤት ልቀቂ ብሎ ማስጠንቀቅ እንደጀመረ አቤቱታ አቅራቢዋ ትናገራለች። አቤቱታ አቅራቢዋ በበኩሏ የቀድሞ የባሏ አሳዳጊ ቤተሰቦች ቤት ሰርተው ከቀበሌ ቤቱ ከመልቀቃቸው በፊት አቶ አበራ እና ወይዘሮ ሰላማዊትን በወረዳው የቤተሰብ ቅጽ እንደቤተሰብ አስመዝግበዋቸው እንደነበርና አሁን ላይ ቤቱ የጋራ ስለሆነ ቤቷን ለቃ የትም እንደማትሄድ ለአቶ እሸቱ እንደነገረችው ትገልጻለች።

የቀበሌ ቤቱ በባለቤቷ እህት ባል ስም ስለነበር እና እነሱ ደግሞ ቤት ሰርተው ሲወጡ እንደልጅ ቤት ውስጥ ይኖሩ ስለነበር የቤቱን ስም ወረዳው በስማቸው እንዲያዞርላቸው ቢጠይቁም ወረዳው ከዛሬ ነገ እያለ ቤቱን በአቤቱታ አቅራቢዋ ስም ሳይዘዋወር ከባለቤቷ ጋር ለፍቺ ይበቃሉ። ከፍቺ በኋለም ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር ያህል በመኝታ ቤቱ ባል፤ በሳሎን ደግሞ ሚስት እና ልጆች ይኖሩ ነበር ።

ይህ በእንዲህ እያለ የቤታቸው ማዕድ ቤቱ በእርጅና ምክንያት ይፈርሳል። ወይዘሮ ሰላማዊትም ማዕድ ቤቱን ለማሰራት በ2013 ዓ.ም ወረዳ አራትን የእድሳት ፈቃድ እንዲሰጣት መጠየቋን ታስረዳለች ። ወረዳውም የእድሳት ፈቃዱን ሰጥቷት የማዕድ ቤቱን ማሳደሷን ታወሳለች።

የእድሳት ፈቃድ የተሰጣቸው በፊት እንደቤተሰብ አብረዋቸው ይኖሩ በነበሩት በአቶ ፍቃዱ ክፍሌ ስም ነበር። ምክንያቱም አቶ ፍቃዱ ቤት ሰርተው ቢለቁም በፊት የቀበሌውን ቤት ከመልቀቃቸው በፊት አቶ ፍቃዱ ወይዘሮ ሰላማዊትን እና ባለቤቷን በቤተሰብነት አስመዝግበው ይኖሩ ስለነበር ነው። ቤቱን በስሟ አዘዋውረው ውል እስከሚዋዋሉ «ስለ» እያለች እየፈረመች በቤቱ መጠቀም የምትፈልገውን እንድትጠቀም ከወረዳው አቅጣጫ ተሰጥቷት ነበር። የቤቱን ኪራይም ስትከፍል የነበረችው ራሷ ነበረች። የውጭ አጥሩም ወድቆ ያሰራችው ወይዘሮ ሰላማዊት መሆኗን ትናገራለች።

ልጆች ሕጻናት ስለሆኑ ከእናታቸው ጋር እንዲኖሩ እና አባት ደግሞ ለልጆች ተቆራጭ እንዲያደርግ በፍርድ ቤት ቢወስንም ከፍርድ በኋላ ባል ለሁለት ዓመታት ያህል ለልጆቹ ተቆራጭ አቆመ።ይህን ተከትሎም ሚስት የቀድሞ ባለቤቷ ተቆራጭ ማቆሙን ለፍርድ ቤት አቤት ትላለች። ፍርድ ቤትም ተከሶ ቀረበ።በዚህም ፍርድ ቤት ተቆራጩን ለምን እንዳቆመ ይጠይቃል። ይህን ተከትሎ ባል ከሳሹን ለመበቀል ፈለገ።የራሱን ሁለት ልጆች እና ከአቤቱታ አቅራቢዋ የመጀመሪያ ባል የምትወለደውን ልጅ ጨምሮ ሶስት ልጆች እያደጉበት ያለውን ቤት ወረዳው እንዲረከበው ለወረዳው ቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት በመሄድ ያመለክታል።

በዚህም ታኅሣሥ 5 ቀን 2013 ዓ.ም የወረዳው ቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት ቤቱን እንድትለቅ ይነግራታል። የወረዳው ቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤትም ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለሕጻን ልጇ እንኳን የሚሆን ጡጦ ማውጣት ሳትችል በዚያኑ እለት ቤቱን በላዩዋ ላይ አሽገውት መሄዳቸውን ትገልጻለች። ቤት በማሸግ ለምን ከቤት ውጭ እባላለሁ? ብላ የወረዳውን ቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊ እንደጠየቀች የምትናገረው አቤቱታ አቅራቢዋ፤ የወረዳው የቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት አስተዳዳሪ የሆነው አቶ አቤል ሳኩሜ ስለጉዳዩ እንደማይመለከተው ገልጾ፤ ጥያቄውን ውድቅ ያደርግባታል። እሺ ልጆቼን

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

ምን ላድርጋቸው? ብላ ለወረዳው የቤቶች አስተዳደር ኃላፊ አቶ አቤል እንደጠየቀች ያስታወሰችው አቤቱታ አቅራቢዋ፤ የወረዳው የቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ አቤልም ስትፈልጊ «ሸጫቸው» ብሎ እንደመለሰላት ትናገራለች።

ቤቱ ከመታሸጉ በፊት ቤቱን ለእድሳት ጠይቃ እንደተፈቀደላት እና በቤቱም ከአምስት ዓመት በላይ እንደቤተሰብ ስለቆየች የወረዳውን ቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤት ቤቱን በስሟ እንዲዞርላት ጠይቃ እንደነበርና በስሟ ለማዘዋወር በሂደት ላይ እያለ ጉዳዩን ይዘውት የነበሩ የወረዳው አመራሮች በሙሉ ከወረዳው መቀየራቸውን ታስረዳለች።

ቤቱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመታሸጉ አማራጭ ያጣቸው አቤቱታ አቅራቢዋ ፤ በታሸገው ቤት ጊቢ ውስጥ ሸራ ዘርግታ ከሶስት ልጆቿ እና ከእናቷ ጋር ብርድና ቁር እየተፈራረቀባቸው መኖር ይጀምራሉ። ምንም እቃ ሳታወጣ ቤቷ መታሸጉን የተመለከቱ የሰፈር ሰዎች ብርድ ልብስ፣ ፍራሽ እና የመሳሰሉትን የእለት መጠቀሚያ እቃዎች እንደሰጧት ትናገራለች። ለአራት ወር ያህል ወረዳው ምንም አይነት ምላሽ ሳይሰጣት ውጭ ላይ ሸራ ወጥራ ኑሮዋን ከልጆቿ ጋር ቀጠለች። ቤቱ በታሸገ በአራተኛ ወር ላይ ያላሰበችው ዱብዳ እንደገጠማት ትገልጻለች።


ከወረዳ አራት ቤቶች አስተዳደር ኃላፊ ቀና ምላሽ ያጣችው አቤቱታ አቅራቢዋ፤ ፍትህን በመሻት ወዲያውኑ ሁከት ይወገድልኝ ስትል ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ የወረዳ አራት ቤቶች አስተዳደርን ከሰሰች። ከሳሽ ለተከሰሰው የቤቶች አስተዳደር የፍርድ ቤት መጥሪያ ለትሰጥ ትሄዳለች ።ይሁን እንጂ ለወረዳው የቤቶች አስተዳደር ለሆነው ለአቶ አቤል መጥሪያውን ስትሰጠው «አልቀበለም» ይላል።በዚህም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት አቅርባ ኃላፊው ተገድዶ ሁለተኛውን መጥሪያ እንደተቀበላት ታስረዳለች።

“ለቤቶች አስተዳደር ኃላፊ አቶ አቤል ለሰባት ጊዜ ያህል የሰው ምስክር በመያዝ እና መጥሪያውን ስለመቀበሉ አስፈርሜ የፍርድ ቤት መጥሪያ ሰጠሁት። ይሁን እንጂ ኃላፊው መጥሪያው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንደሆነ እያወቀ አንድም ቀን ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ቀረ። ፍርድ ቤቱም መጥሪያውን ተቀብሎ ፍርድ ቤት መቅረብ ባልቻለው በአቶ አቤል ላይ ምንም አይነት እርምጃ ሳይወስድ ቀረ፡፡» ትላለች።

ኃላፊው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ የማያስገድድ ከሆነ ቢያንስ ቤቱን ለሌላ ሰው እንዳይሰጥባት በማሰብ የእግድ ደብዳቤ ፍርድ ቤቱ እንዲሰጣት መጠየቋን የተናገረችው አቤቱታ አቅራቢዋ ፤ ፍርድ ቤትም መጋቢት 7 ቀን 2013 ዓ.ም የእግድ ደብዳቤ እንደሰጣት እና ይህን የእግድ ደብዳቤ ለወረዳው የቤቶች ኃላፊ ማስገባቷን ታስታውሳለች ።

እንደ አቤቱታ አቅራቢዋ ገለጻ፤ ሚያዚያ 29 ቀን የፍርድ ቤት ቀጠሮ ነበራቸው ። በዚህ ቀን የወረዳው የቤቶች አስተዳደር አቶ አቤል ስልክ ደውሎ «ክሱን አቁሚ፤ ክርክሩን መሸነፍሽ የማይቀር ነው!» ሲል ይዝትባታል። እንደተለመደውም አቶ አቤል በቀጠሮው ቀን ሳይቀርብ ቀረ። ለዳኛውም «ክሱን አቋርጪ ብሎ እንደደወለላት ስታስረዳ» ዳኛውም «አንች ምን ትያለሽ» እንዳላትና እሷም «ክስ የማቋርጠው ምን ይገኜ ነው?» ብላ ለዳኛው ጥያቄውን በጥያቄ ትመልሳለች። ፍርድ ቤቱም በድጋሚ ለግንቦት 10 ቀን 2013 ዓ.ም ቀጠረ። በቀጠሮውም ቀን አቶ አቤል መገኘቱን ታስረዳለች።

በወቅቱም አቶ አቤል እግድ ላይ ያለው ቤት አዲስ ውል የተገባበት መሆኑን ገለጸ። ፍርድ ቤትም «እግድ ላይ ያለ ቤት ለምን አዋዋልክ?» ተብሎ ተጠየቀ፤ ውል ያዋዋለውም የእግድ ደብዳቤ ከፍርድ ቤት ከመምጣቱ አንድ ወር ቀደም ብሎ በስድስተኛው ወር መሆኑን ለፍርድ ቤቱ አስረዳ። ቤቱ የተሰጠው መጋቢት 7ቀን 2013 ዓ.ም የፍርድ ቤት እግድ ለወረዳው ቤቶች አስተዳደር ጽህፍት ቤት ካስገባች በኋላ የፖሊስ አባል ለሆነ ግለሰብ መሆኑን የምትገልጸው አቤቱታ አቅራቢዋ ፤ እግድ ያስገባች እለት የድሃ ድሃ ነው ተብሎ ቤቱን ተዋዋለ የተባለው ሰው የመንግሥት ደሞዝተኛና የፖሊስ አባል መሆኑን ትናገራለች። የፍርድ ቤት እግድ ለወረዳው ቤቶች አስተዳደር መግባቱን የሰማው ፖሊስ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በግብረ ኃይል መጥቶ አቤቱታ አቅራቢዋ በሌለችበት የታሸገውን ቤት በመስበር




አረብ አገር ሰርታ ያፈራችውን ሙሉ የቤት እቃ ጭኖ መውሰዱን ታስረዳለች።

አቤቱታ አቅራቢዋ ንብረቷ ወዴት ተጭኖ እንደተወሰደም መረጃ እንዳልነበራት ጠቁማ፤ በድጋሚ በመጋቢት 20 ቀን 2013 ዓ.ም ቤቱን ከወረዳው የቤቶች አስተዳደር ጋር ተዋውየዋለሁ የሚለው የፖሊስ አባል ፤ ሸራ ወጥራ ትኖርበት የነበረውን መጠለያ በማፈራስ ሙሉ እቃውን ለሁለተኛ ጊዜ ጭኖ ወሰደ። ይህን ተከትሎ አቤቱታ አቅራቢዋ ከሶስት ልጆቿ ጋር ጎዳና መውጣቷን ሲቃ እያናቃት ተናግራለች። ፖሊሱን «አንተ የሕግ ሰው ነህ፤ የፍርድ ቤት እግድ እያለ እንዴት እቃዬን የትም ጥለህ ወደ ቤት ልትገባ ቻልክ?» ብላ መጠየቋን የምትናገራው አቤቱታ አቅራቢዋ፤ «እግድ ቢኖረው ባይኖረው እኔን አይመለከተኝም» ሲል ፖሊሱ እንደመለሰላት ጠቁማለች።

ይሄን ተከትሎ የእግዱን ወረቀት ይዛ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ትሄዳለች። እግዱን ከምንም ሳይቆጥር በእግድ ወደተያዘው ቤት የገባው ፖሊስ እዚያው አካባቢ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ይሰራ ስለነበር እግዱን ፖሊስ እንዲያስጠብቁላት ብትናገርም «ቤቱ ለእሱ ተሰጥቶታል። የእሱ ችግር አይደለም ወረዳውን አናግሪ» ብለው እንደመለሷት እና የፍርድ ቤቱን እግድ ለማስጠበቅ ፍላጎት የነበረው ፖሊስ ማጣቷን ትገልጻለች።

**የወረቀት ሰነዶች**

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የነዋሪዎች መመዝገቢያ ቅጽ ላይ እንደተመለከተው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት የቤት ቁጥር 505 በአቶ ፍቃዱ ክፍሌ የተመዘገበ ቤት ውስጥ ስድስት ግለሰቦች በቤተሰብ አባልነት የተመዘገቡ ሲሆን ወይዘሮ ሰላማዊት ሃብታሙ ስመሪ አንዷ የቤተሰቡ አባል እንደሆነች ተጠቅሷል። ሌላው የሰነድ ማስረጃ ደግሞ በቁጥር አ/ከ/ ወስ/5690/13 በቀን 07/05/2013 ዓ.ም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ አራት የወሳኝ ኩነት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የተጻፈው ነው ። በዚህ ደብዳቤ ላይም ወይዘሮ ሰላማዊት ሃብታሙ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ቀበሌ 17 የቤት ቁጥር 505 ነዋሪ መሆኗን ያረጋግጣል። ከዚህ በተጨማሪ ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት በ18/05/2012 ዓ.ም የተሰጠ የአዲስ አበባ የነዋሪነት መታወቂያ እንደሚያመላክተው ወይዘሮ ሰላማዊት ሃብታሙ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ቀበሌ 17 ነዋሪ መሆኗን ያሳያል። ከዚህ ባሻገር ወይዘሮ ሰላማዊት በየካቲት ወር 2007 ዓ.ም ለልጇ የልደት ካርድ ስታሰራ የተሰራላት በዚሁ የቤት ቁጥር ነው። ከሸማቾች ዘይት እና መሰል ሸቀጦችን ለመግዛት የምትጠቀምበትም በዚሁ ቤት የተሰጣትን መታወቂያ መሰረት አድርገው ነው ። በ2010 ዓ.ም ወይዘሮ ሰላማዊት ሶስተኛ ልጇን ስትወልድ የወረዳው የወሳኝ ኩነት የልደት ሰርተፊኬት የሰጠውም በዚሁ የቤት ቁጥር ነው። በህዳር 3 ቀን 2013 ዓ.ም በአቶ ፍቃዱ ስም የእድሳት ፈቃድ ወስዳ የማእድ ቤቱን ያሳደሰችው ወይዘሮ ሰላማዊት ነበረች።

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት መመሪያ**

ከተማ አስተዳደሩ በ2011 ዓ.ም ባወጣው መመሪያ መሰረት የቀበሌ ቤቶችን ለሶስተኛ ወገን በምን አይነት መልክ ማስተላለፍ እንደሚቻል ያትታል። በዚህ መሰረት በመመሪያው ክፍል ሶስት ቁጥር 15 ንዑስ ቁጥር አንድ ከ«ሀ» እስከ «ሠ» በግልጽ ተመላክቷል። በተለይም ደግሞ በመመሪያው ክፍል ሶስት ቁጥር 15 ንዑስ ቁጥር አንድ ለ፣ሐ እና መ የአቤቱታ አቅራቢዋን ጉዳይ በቀጥታ ይዳስሳል። በመመሪያው ክፍል ሶስት ቁጥር 15 ንዑስ ቁጥር አንድ እንደተመላከተው የቀበሌ ቤትን የተከራየ ማንኛውም ሰው በሞት ሲለይ ወይም ከአካባቢው በተለያየ ምክንያት ሲለቅ ቤቱን ለቢሮው እንዲመለስ ይደረጋል። ሆኖም ሚች በተከራየው ቤት ውስጥ፡-

ሀ. የተከራይ ባል ወይም ሚስት ለመሆኑ ሕጋዊ የጋብቻ ማስረጃ ሲያቀርብ ፤

ለ.የተከራይ ልጆች እና በሕጋዊ መንገድ በጉዲፈቻ ያደጉ ልጆች፤

ሐ. ከልጅነታቸው ጀምሮ ከወላጆቻቸው ተለይተው እንደ ልጅ በቤት ውስጥ መኖራቸው በወረዳው የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ ውስጥ መመዝገቡ ሲረጋገጥ እና የወረዳው አስተዳደርም እንደልጅ ቤት ውስጥ ማደጉን ሲያረጋግጥ ፤

መ. በችግር ምክንያት ከተከራይ ጋር በጥገኝነት የሚኖሩ የባል ወይም የሚስት እናት ወይም አባት ለመሆናቸው በወረዳው አስተዳደር ሲረጋገጥ እንዲሁም ሁሉም ወራሾች ስለመሆናቸው እና በስማቸው የግል መኖሪያ ቤት የሌላቸው ወይም ከዚህ በፊት በሽያጭ ወይንም ከመንግሥት የተከራዩት ቤት የሌላቸው ወይም ከዚህ በፊት በሽያጭ ወይንም በስጦታ ያላስተላለፉ መሆኑ በመስረጃ ሲረጋገጥ ቤቱን በቀድሞ ኪራይ ተመን መሰረት በአዲስ ውል እንዲከራዩ ሊፈቀድላቸው ይችላል ሲል ያትታል። በዚህ መሰረት አቤቱታ አቅራቢዋ ሕገ ወጥ ነሽ ተብላ ከቤት እንድትወጣ መደረጉ ምን ያህል ሕግን የተከተለ ይሆን ? ፍርዱን ለአንባብያን እንተዋለን።

**የወረዳ አራት ስራ አስፈጻሚ ምላሽ**

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የወረዳ አራት ስራ አስፈጻሚን ስለጉዳዩ ጠይቋል። ስራ አስፈጻሚው አቶ ዳዊት ብርሃኑ እንደሚገልጹት፤ አቤቱታ አቅራቢዋን የሚያውቋት የቤት እቃዋ ተጭኖ ወደ ወረዳው መጥተው ከተከማቸ በኋላ ነው። የቤት እቃዋ እንዲሰጣት በጠየቀች ጊዜ እንዲሰጣ አድርገዋል።

የዝግጅት ክፍሉ በ 2011 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ክፍል ሶስት ቁጥር 15 ንዑስ ቁጥር 1 ከሀ-ሠ ባሉት መመሪያዎች ቤቱን ልታገኝ አትችልም ነበር ወይ? በሚል ላቀረበላቸው ጥያቄ ስራ አስፈጻሚው ሲመልሱ፤ በመመሪያው ላይ እንደተመላከተው በጉዲፈቻ ወይም በደባልነት ወይም በልጅነት በወረዳው የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ ቢመዘገቡም ወረዳው በጉዲፈቻነት ወይም በደባልነት ወይም በልጅነት ስለማደጋቸው ወይም ስለመኖራቸው ማረጋገጫ ካልሰጠ ሶስተኛው ወገን በቤቱ የመጠቀም መብት የለውም የሚል ምላሽ ሠጥተዋል።

የወይዘሮ ሰላማዊት ባለቤት የነበረው አቶ እሸቱ እንደልጅ ያደገው በዚህ ቤት ነው። ወይዘሮ ሰላማዊትም ያገባት በዚህ ቤት እያለ ነው ። ስለዚህ እነኝህ ሰዎች ከመመሪያው አንጻር በቤቱ ተጠቃሚ የማይሆኑበት ምን የሕግ አግባብ አለ? በማለት የዝግጅት ክፍሉ ላቀረበው ጥያቄም የወረዳው ስራ አስፈጻሚ የሚከተለውን ምለሽ ሰጥተውናል።የወይዘሮ ሰላማዊት የቀድሞ ባለቤት በቤቱ ውስጥ ቢያድግም በወረዳው እስካልተረጋገጠ ድረስ እንደ ሶስተኛ ወገን ቤቱን ወራሽ መሆን አይችሉም ። ምክንያቱም በአንድ ቤት ዘመድ ወይም ጎረቤት ስለሆነ ብቻ የቤት ውል ያላቸው ሰዎች ለመታወቂያ ሲሉ እንደቤተሰብ ሊመዘግቡ ይችላሉ። ስለዚህ በቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ ቢመዘገብም ወረዳው ማረጋገጫ እስካልሰጠው ድረስ አንድን የቀበሌ ቤት በሶስተኛ ወገንነት ሊወርስ አይችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ጨምረውም «እኛ ቤቱን ያዋዋልነው ለአቶ ፍቃዱ ክፍሌ ነው። ኪራይም እየተከፈለ ያለው በአቶ ፍቃዱ ስም ነው ። ስለዚህ ከአቶ ፈቃዱ ውጭ ለሌላ ሰው እኛ አላዋዋልንም።» ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

በዝግጅት ክፍሉ የምርመራ ጋዜጠኛ፤ እነ አቶ ፍቃዱ ክፍሌ ቤት ሰርተው ከወጡ ከአምስት ዓመት በላይ ሆኗቸዋል።የቤቶች አስተዳደር ደግሞ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቤቶቹን በአካል ተገኝቶ ቁጥጥር እንደሚያደርግ ይታወቃል። ታዲያ እናንተ አቶ ፍቃዱን ብቻ የምታውቁ ከሆነ ከአምስት ዓመታት በላይ እነ ወይዘሮ ሰላማዊት በቤቱ እንዲቆዩ ለምን ተፈቀደላቸው? በሚል ላቀረበው ጥያቄ፤ እሱን ጥያቄ መጠየቅ የሚገባው «በወቅቱ የነበሩ አካላትን ነው» የሚል ምላሽን የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ሰጥተዋል።

ሌላው የዝግጅት ክፍሉ ለወረዳው ስራ አስፈጻሚ ያነሳው ጥያቄ የወረዳው ቤቶች አስተዳደር ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ በአንድ ቀን ቤቱን ልቀቂ ብሎ በአንድ ቀን ቤቱን የማሸግ መብት አለው ወይ? የሚል ሲሆን፤ የወረዳው ስራ አስፈጻሚ በበኩሉ፤ «ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የማሸግ መብት የለውም። የወረዳው ስራ አስፈጻሚ ይህን አድርጎ ከሆነ ስህተት ነው» ብለዋል ። የወይዘሮ ሰላማዊት ጉዳይ የሆነው እንደዚህ ነው። ስለዚህ ምን ይላሉ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄም፤ የወረዳ ስራ አስፈጻሚ «አዲስ ስለሆንኩ ስለጉዳዩ የማውቀው ነገር የለም» የሚል ምላሽ ሰጥተውናል።

የዝግጅት ክፍሉ በተጨማሪ ቤቱን ለሌላ ሰው ያዋዋላችሁት በፍርድ ቤት ክርክር ላይ እያለ ነው። በፍርድ ቤት ላይ ክርክር ላይ ያለን ቤት ማዋዋል ይቻላል ወይ? በሚል ላቀረበው ጥያቄ «በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ያለን ቤት የፍርድ ቤት ክርክሩ ሳያበቃ መዋዋል ወንጀል ነው »የሚል ምላሽ ሠጥተዋል። የወይዘሮ ሰላማዊት ጉዳይ ግን የሆነው እንደዚህ ነው። ስለዚህ ምን ይላሉ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄም «እኔ አዲስ ስለሆንኩ የማውቀው ነገር የለኝም። » ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ወይዘሮ ሰላማዊት ቤት ለማደስ ፈልገው «ስለ» ብለው እየፈረሙ ቤታቸውን ማደሳቸውን ሰነዶች ይጠቁማሉ። ስለዚህ ምን ይላሉ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄም የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ሲመልሱ «ህጋዊ ውክልና ካላት «ስለ» ብላ ቤቱን ማሳደስ ትችላለች። ነገር ግን የቤተሰብ አባል ስለሆነች ብቻ «ስለ» ብላ ፈርማ ቤት ማደስ አትችልም። ይሄን የፈቀደ አመራር ካለ ሕገወጥ ስለሆነ በሕጉ መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል» ብለዋል።

ወይዘሮ ሰላማዊት ከቤት የወጣችበት አግባብ ትክክለኛ ሂደትን ያልጠበቀ ነው። ወይዘሮ ሰላማዊት ደግሞ የድሃ ድሃ ከሚባሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች አንዷ ናት ። የተወሰደባትን ቤት ራሱን ባታገኝም እንኳን ለዚህች ግለሰብ ወደፊት ምን ልታደርጉላት ትችላላችሁ? በሚል ጥያቄ ያቀረብን ሲሆን፤ በምላሻቸው «የወይዘሮ ሰላማዊትን የኑሮ ደረጃ በሕዝብ አስገምግመን እና አስተችተን ቤት የምታገኝበትን ሁኔታ እናጤናለን »ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

በመጨሻም ከወይዘሮ ሰላማዊት ጋር ተያይዞ በቀጣይ ዝግጅት ክፍል የክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደርን እና የክፍለ ከተማውን ስራ አስፈጻሚ ምላሽ ይዘን የምንቀርብ ይሆናል እስከዚያው ቸር እንሰንበት።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# ከዛሬው በደላችን የነገው ኩነኔያችን

ለገለልተኝነት የማንታማ በርካታ ዜጎች የፖለቲካውንና የፖለቲከኞችን ጉዳይ አብጠርጥረን፣ ፈትነንና ፈትገን ገለባው በርክቶ የሚያጠግብ ፍሬ ስላጣንበት ባለጉዳዮቹ በእጃቸውና በአፋቸው የሚያሽሞነሙኗቸውን "የሥልጣን መናጠቂያ ሰነዶቻቸውን (ፕሮግራሞቻቸውን)" በሰንዱቅ ውስጥ አሽገን ካስቀመጥን ሰነባብቷል። አንዳንድ እርባና ቢስ "ማኒፌስቶዎችንም" በገለጥናቸው ጊዜ ሁሉ ከሚያበግኑንና ከሚያሾፉብን ብለን እንደሚሆን እንደሚሆን አድርገናቸዋል። ምክንያቱም በሰነዶቹም ሆነ በሰናጆቹ ሕይወት ውስጥ ምሳሌነትና ተስፋ ስላጣንባቸው ምን ይሉት ሞራል ኖሮን "ይደልዎ" እያልን እናሞካሻቸዋለን?

"ትልቁ የሕገ መንግሥት መጽሐፍ ተብዬውም" ቢሆን "ቄሱም ዝም፣ መጽሐፉም ዝም" እንዲሉ፤ መከራና አሳር ገጥሞን አዬዬ እያልን ለትድግና ስንጮኽበት የማይመልስ ዲዳ፣ የማይራመድ ሽባ፣ የማይወስን ፈሪ፣ ጨክነን ብለው ሲቆጡት ደግሞ "እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ" እያለ "ዱታ ነኝ ባይ" መሆኑ፣ አቅምህን አሳየን እያሉት እድል ሲሰጡት ደግሞ "ልፍስፍስ" እያለ "ካብ አይገባ ድንጋይ ስለሚሆንብን" በዚያም ብንል በዚህ ተስፋ አጥተን ግራ መጋባት ውስጥ ስለተዘፈቅን "ለጊዜ ጊዜ በመስጠት" ከገጾቹ ጋር ተኳርፈን ዓይናችንን ከገጾቹ ላይ ካነሳን ሰነባብቷል።

ከላይ የተጠቀምንባቸው ቃላት በእጅ የተቀረጸ ጣኦትን የሚሄስ አንድ ግጥም ያስታውሰናል። ከስንኙ ውስጥ አንድ ቃል ብቻ ለውጠን እንጥቀሰው፡-

**[ሰነዳቸው] ዐይን አለው አያይም፣**
**አፍ አለው አያውራም፣ ጆሮ አለው አይሰማም።**
**እርሱንም ሁሴ ይሸከሙታል፣**
**ወደዚያ ወደዚህ ያረጉታል...**

(ግጥሙ አልተጠናቀቀም)

ለምን እንዲህ መረር ለማለት እንደተፈለገ ከራሱ ከሰነዱ እየጠቀስን በምሳሌ እናስረዳ። "ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው - አንቀጽ 18፡1" እና አንቀጽ 24 ላይ ደግሞ "1. ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው፣ 2. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው፣ 3. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ስፍራ በሰብዓዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው" የሚሉትና በአንቀጽ 28 ላይ የተዘረዘሩትን "በስብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች" የሚለውን "በቃላት ተቆንጃጅቶ ለተግባር የኮሰመነውን" ክፍል እንዳለ ብንዘከዝከው ብዙ ሰዎችን ስለሚያበሳጭ ያለመነካካቱን መርጠናል። "የወረቀት ነብር" የሚለው አባባል ይታወስ።

ወዲያም ብንቃብዝ ወዲህ፤ "በሰዎች አእምሮ የተደረሱ ሰንዶች" ህመም ላይ የጣለንን ወቅታዊ ሀገራዊ ደዌ በቃላት ቅባት ማበስ ካልሆነ በስተቀር ሰንኮፉን ነቅለው ሊፈውሱልን ስላልቻሉ ፊታችንን ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ለመመለስ ግድ ይለናል። ለምን ቢሉ፡- ዘጠና ዘጠኝ ከምንትስ ፐርሰንት ዜጎቿ "ተግባሩ እንኳን ቢቀር፣ ለወጉ ያህል የእምነት ቤተሰቦች ናቸው" በማለት ሀገራዊው እስታትስቲክስ "ሊያቄለንም ይሁን ሊያደፋፍረን" እቅጩን ስለሚነግረን "በዓለማዊው መንግሥታዊ ሚዲያዎች ላይ የቅዱሳት መጻሕፍት ምክሮች" እንዲስተናገዱ የብረት በሩ መከፈት አለበት።

"ምን ሲደረግ!" የሚሉ ተቆጭዎች "ዘራፍ የሚሉ" ከሆነም "እንደየእምነታችን በሕዝባዊ ሚዲያዎች ላይ መጽናናትን አትከልክሉን" በማለት "በሕግ አምላክ! በጉልበት አምላክ! ወይንም በእውነት አምላክ!" እያልን በመማጸን አደብ እንዲገዙ ብንጠይቅ ተዳፈራችሁ ልንባል አይገባም። ሌላ ተስፋ የሚያሳዩን ከሆነም እሰየው እንዲያመላክቱን ልባችንንም፣ ዓይናችንንም ሆነ ጆሯችንን እንከፍትላቸዋለን።

ይህንን መሰሉን ተማጽኗችንን የሚያከብሩ ከሆነ ይህ ጸሐፊ ብቻም ሳይሆን ሌሎቹ የዚህ ጋዜጣ ቤተኞችም አልፎ አልፎም ቢሆን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በየእምነታችን እየተከባበርን የሚያንጹንን፣ ከክፋትና ከጭካኔ የሚከለክሉንን፣ ልጓሙን ለቆ የሚጋልበው ቀልብያችንም አደብ ገዝቶ እንዲሰክን የሚመክሩ አናቅጽን ቢያስታውሱን አይከፋም። ወደ መልካምነት የሚመሩን፣ በትንሽ በትልቁ ምክንያትም ሽንቁር የበዛበትን የሀገራችንን ወቅታዊ መጠፋፋትና አሳፋሪ ገመናዎች እንድንደፍን ቢያስተምሩን ጽድቅም በጎነትም እንደሆነ ሊታመን ይገባል። በዚሁ መሠረትም በዛሬው ጽሑፍ ህሊናችንን የሚሞግት አንድ አንቀጽ ከቅዱስ መጽሐፍ ጠቅሰን እንንደረደራለን፡-

"እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው። ሰባተኛውንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች። ትዕቢተኛ ዓይንን፣ ሐሰተኛ ምላስን፣ ንጹሕ ደምን የሚያፈሱ እጆችን፣ ክፉ ሃሳብን የሚያውጠነጥን ልብን፣ ወደ ክፋት የሚቻኮሉ እግሮችን፣ በውሸት ላይ ውሸት የሚጨምር ሃሰተኛ ምስክርን፣ በወንድማማቾች መካከል ጠብን የሚዘራ ሰውን።" (ምሳሌ 6፡16 - 19)።

ፈጣሪ የተጠየፋቸው እነዚህ ሰባት የደደሩ በደሎችና ኃጢያቶች ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈሉን፣ ለመከራ እንደዳረጉንና የእምባ ምክንያት እንደሆኑን ብዙዎቻችን ምስክሮች ነን። ምስክርነቱን ሰፋ እናድርገው ከተባለም የውጤቶቹን ገፈት በነጋ በጠባ የሚጎነጨውን ሕዝብ በጅምላ ዋቢ መጥራት ይቻላል።

በትዕቢተኛ ዓይን የተጠቁ፣ በሐሰተኛ ምላስ ተነድፈው ፍትሕ የተዘባባቸው፣ ንጹሕ ደም ባፈሰሱ እጆች መከራ የወደቀባቸው፣ ክፉ ሃሳብ ሲያውጠነጥኑ አድረው የብዙዎችን ቤት ያዘጉና ተስፋቸውን ያመከኑ፣ በክፋት በተበከሉ እግሮች እየተሸቀዳደሙና በማደነቃቀፍ የበርካቶችን ሩጫ መና ያስቀሩ፣ በዋሾዎች ምስክርነት ኑሮና ሕይወት የተመሰቃቀለባቸው፣ በወንድማማቾች መካከል የጠብ አሜከላ እየዘሩ ደም ያቃቡና ያጫረሱ ብዙዎች ናቸው። ከፍ ሲልም በእነዚህ እኩይ የማሕበረሰብ አራሙቻዎች ጥቁር ከል የለበሰችው ሀገር ራሷ ናት።

መልካቸው የተዥጎረጎረው እኒህን መሰል የአመጽና የበደል ተግባራት ከትናንት ይልቅ ዛሬ፣ ከአምና ይልቅ ዘንድሮ በግላጭ እያስተዋልን ብቻ ሳይሆን ጥቃቱ አይሎብን ሕይወት መሮብናል። ግፉን ለመሸከምም ወገባችን ጎብጧል። በእውነት እነዚህን የከፉ በደሎችና ግፎች የፈጣሪ ዓይኖች እያስተዋሉ ጆሮውም የግፉዓንን እሪታ እየሰማ ታግሶ ዝም ይላልን? በፍጹም። የፈጣሪ ፍርዱ ይዘገይ ካልሆነ በስተቀር ይቀራል ማለት የአምላካዊ ባህርይው መገለጫ አይደለም። የምድራዊ በደል ፍጻሜ በዘለዓለማዊ ኩነኔ እንደሚጠናቀቅ የየትኞቹም እምነቶች ቅዱሳን መጻሕፍት አስረግጠው የሚያስተምሩት አይቀሬ እውነታ ስለሆነ ጥርጥር አይገባንም።

የኢስላም ሃይማኖት መምህራን "ተውበት - "ወደ አላህ መመለስ" የሚለውን የሃይማኖት መርህ የሚያብራሩት እንዲህ በማለት ነው። "የኢማንን (ልባዊ የሆነ እምነት ማለት ነው) ጥንካሬ ከሚፈጥሩት ውስጥ በጣም አስፈላጊውና ተቀዳሚው ተውበት ወይንም ወደ ፈጣሪ ለመመለስ መወሰን ዋነኛው ጉዳይ ነው። ኃጢአትን የማያከብድ፣ ነውርን የማይገልጥ፣ ለዚህም ዋጋ የማይጠየቅበት መሠረታዊ እውነታው ወደ ፈጣሪ ተመልሶ ከኃጢያትና ከበደል መራቅ ነው።

"ተውበት" የፈጣሪን ተውፊቅ (እገዛና ብርታት) የሚፈልግ ቢሆንም የሚከብድ ግን አይደለም። ከአማኙ የሚጠበቀው ከስህተት መመለስ፣ ከጥፋት መጸጸት፣ ዳግም በደል ላለመፈጸም መወሰን ብቻ ነው። ከክፋት መራቅ፣ ለወንድማማች ጠብ ምክንያት ያለ መሆን፣ ፍትሕንና ርትእን በማጓደል በደልን በራስ ላይ ያለማንገስ በላጺስ የሚመሰሉ ናቸው፤ በኃጢአት የቆሸሸና ያደፈ ነፍስን ለማጽዳት ኃይል አላቸውና።" በማለት አስተምህሮው ይመክረናል። የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ እንደተከበረ ሆኖ የህሊናችንም ድርሻ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ህሊናችን "የፈጣሪን እውነት ለመግለጽ ውክልና ወስዷል" እየተባለ በተለምዶ መነገሩም ስለዚሁ ነው።

በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ውሎ አምሽቷችን ውስጥ የምናስተውላቸውና የምናደምጣቸው በርካታ ጉዳዮች ጆሯችንን ጭው ከማድረግ አልፈው ለድንዛዜም ምክንያት ሆነውናል። በቅርቡ በነበረው የፓርላማ ውሎ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ (ዶ/ር) የሕዝብን ጸጥታ እንዲያስከብሩ በትከሻቸው ላይ ከፍተኛ ሀገራዊ አደራ የወደቀባቸው አንዳንድ የጸጥታ ክፍል ባልደረቦችና ለፍትሕ አካላት ቤተኛ የሆኑ ግለሰቦች እጃቸውና ህሊናቸው ንጹሕ እንዳልሆነ በግልጽ ቋንቋ አረጋግጠውልናል። ምንም እንኳን የልቅሷችን ዋና ሰበቦች ከሆኑ ቢሰነባብቱም።

የፍትሕና የርትእ ምንጩ የደፈረሰ ከሆነ ሌላው ሀገራዊ ጉዳያችን እንዴት ኩልል ብሎ ሊጠራ ይችላል? ችግሮቻችን ሊከፉብን የቻሉት ነገራችን ሁሉ "ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ፤ ውሃ ቢያንቅ በምን ይውጡ" ብጤ ስለሆነብን ሳይሆን አይቀረም።

አንድ ሀገራዊ ተስፋ ብልጭ ብሎ እኛ ዜጎችም በደስታ እየተፍነከነክን "ጥርሳችንን ብልጭ" ማድረግ ገና ስንጀምር ለእምባና ለኀዘን የሚዳርጉ ችግሮች ተግተልትለው ከፊታችን ይገሸራሉ። "በቅንነትና በታማኝነት" ሕዝብን ለማገልገል በአደባባይ መሃላ ገብተው በሥልጣን ወንበር ላይ ፊጥ ያሉ "ባለጊዜዎች" ሳይውሉ ሳያድሩ የአስመሳይነት ካባቸውን አውልቀው "ለሆድና ለነፍሳቸው" ማሸርገድን ስራዬ ብለው ይያያዙታል። ቃል የእምነት ዕዳ መሆኑን ዘንግተው ቃል ለራስ የሚቆርሱት እንጀራ እንደሆነ በመቁጠር ለነፍሳቸው ብቻ ሲዳከሩ ይስተዋላል።

አንዳንዱ ተመርጦ የሕዝብ ወኪል እስኪባል ድረስ በጠባይም ሆነ በግብር ፊት ፊት እየቀደመ "ከሰል ካላነጣሁ፤ ወተት ካላጠቆርኩ" እያለ ማማለሉን ይችልበታል። ተመርጦ የሕዝብ አደራ በተሸከመ ማግስት ግን "የተውኔት ካባውን አውልቆ" የውስጥ ምኞቱን ገመና ይፋ በመግለጥ ኑሮውን ሊያደላድል ይርመጠመጣል። ከሰኔ እስከ ሰኔ አጃኢብ ካሰኙንና "ዘንድሮ፣ ዘንድሮ" እያልን እንድናንጎራጉር ምክንያት ከሆኑን ጉዳዮች መካከል አንዱ ይህ ትዝብት ነው።

**"ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣**
**የስንቱ ተወርቶ፣ የስንቱ ተነግሮ - ዘንድሮ።**
**በዚያኛው ተገርመን ጥቂት ሳንቆይ፣**
**የዚህኛው መባስ አያስቆጭም ወይ።"**

ብለን እምባ በተቀላቀለበት መነፋረቅ አንድንቆዝም የተገደድንበት አንዱ ብሶት የሚገለጸው በዚህ መልኩ ነው።


በአንድ የግል ገጠመኝ ጉዳዩን ለማሳየት ልሞክር። ይህ ጸሐፊ "እኛን ለመወከል ስለሚመጥኑ ድምጻችንን አንንፈጋቸው" በማለት ለብዙ ወዳጆቹ ቅስቀሳ ካደረገላቸው አንዱ "የተከበሩ" የሚለውን ክብር ከተጎናጸፈ በኋላ፤ "ሀገርና ሕዝብን አደጋ ላይ የሚጥለውን ይህንን ጉዳይ ለሚመለከተው ክፍል በፍጥነት አድርሰህ መፍትሔ ይፈለግለት" ብሎ ሲያማክረው (ያውም ከብዙ የስልክ ሙከራ በኋላ) በድምጹ ውስጥ ሥልጣኑን እየገለጸ የሰጠው መልስ፤ "ምን ያስደንቃል ሀገሪቷ ውስጥ እኮ ከዚህም የከፉ በርካታ ችግሮች ሞልተዋል። ሊገርመን አይገባም" የሚል ነበር።

እርግጥ ነው ሀገሬ ወደፊት እንዳትገሰግስ በየጎዳናዎቿ ላይ "የአረንቋ ሐይቆች" እያሰነካከሉ ጉዞዋን ለመግታት እንደሚሞክሩ እያየንና እየሰማን ነው። የውጭ ጠላቶቻችን የሚወረውሩብን የጥፋት ቋጥኞች ለሕዝብ የሚገለጡት ከመከኑ በኋላ እንጂ በነጋ በጠባ "ይህንና ይህንን የመሳሰሉ ሴራዎች እየተሞከሩብን ነው" እየተባለ ቢገለጽ ኖሮ ድብርት ውስጥ ይከተን ነበር።

ይህም ያነሰ ይመስል በዘርና በብሔር ተኮር እየተፈጸመ ያለው የልጆቿ እልቂት ሀገሬን እንደ ቅዱስ መጽሐፏ ራሄል "እንባዋን ወደ ጸባኦት እንድትረጭ" ግድ ብሏታል። በዚህም ምክንያት እስከ ዛሬም ድረስ የኀዘን ጨርቋን እንኳን ለመቀየር ፋታ አላገኘችም። እርግጥ ነው እንደ ሕዝብ ከውስጥና ከውጭ ፋታ የሚነሱን በርካታ ወጀቦች ቢያስገመግሙም ችግሮቻችን ጊዜያዊ እንጂ በቋሚነት ስለማይዘልቁ ኢትዮጵያም ሆነች ሕዝቧ እንዳነቡ አይኖሩም። ለዚህ ነው ወደ ቀልባችን ተመልሰን ከበደል እጃችንን እናንጻ፤ ከመጻኢ ኩነኔም እንጠበቅና የየድርሻችንን ኃላፊነት እንወጣ የሚል ምክር ለመወርወር የተገደድነው። ሰላም ይሁን!

# የነዳጅ ድጎማ መነሳትና የኑሮ ውድነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ኢትዮጵያ ከምታመርታቸው የግብርና ምርቶች መካከል ቡና እንዲሁም የቅባት እህሎችን ጨምሮ ሌሎችንም ወደ ውጭ አገራት ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ታገኛለች።ይሁን እንጂ ነዳጅን ጨምሮ በአገር ውስጥ ተኪ የሌላቸው የተለያዩ ምርቶችን ደግሞ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የምታስገባ አገር ናት።በመሆኑም መንግሥት በማንኛውም መንገድ የሚያገኘውን የውጭ ምንዛሪ በአብዛኛው ለነዳጅ ግዢ የሚያውል መሆኑም ይታወቃል።

ኢትዮጵያ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ ከምታስገባቸው ምርቶች መካከል ቀዳሚውን ድርሻ የሚይዘውና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን የሚጠይቀው ነዳጅ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት የመንግሥትን ኢኮኖሚያዊ አቅም ከመፈታተን ባለፈ ወገቡን እያጎበጠው የመጣ ከፍተኛ ወጪ እንደሆነ ይታመናል።በተለይም በአሁኑ ወቅት መንግሥት በአንድ ወር ውስጥ ብቻ እስከ 12 ቢሊዮን ብር ዕዳ ተሸክሞ ነዳጅን ወደ አገር ውስጥ እያስገባ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በኢትዮጵያ ያለው የነዳጅ ምርቶች ዋጋ ከጎረቤት አገራት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ መሆኑን በማንሳት ይህም ምርቱን ለህገ ወጥ ንግድ እንዳጋለጠው፣ በጥቁር ገበያ እንዲቸበቸብና በተለያየ መንገድ ነዳጅ ከአገር ውጭ እንዲወጣ ምክንያት እንደሆነ የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን የሥራ ኃላፊዎች ገልጸው፤ ለዚህም መንግሥት ለነዳጅ ድጎማ የሚያወጣውን ከፍተኛ ወጪ ለመቀነስ በጥናት የታለመ የነዳጅ ድጎማን እንደ መፍትሔ አስቀምጧል ይላሉ።

ታዲያ መንግሥት መፍትሔ ነው ያለውን የታለመ የነዳጅ ድጎማን ሲያነሳ አሁን ያለውን የኑሮ ውድነት ይበልጥ እንዳያባብሰውና ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች እንዳይፈጠሩ ምን መደረግ አለበት ስንል ላነሳነው ጥያቄ የምጣኔ ሀብት ምሁራን ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ አንጻር ነዳጅ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሸጥበት ዋጋ እርካሽ መሆኑን የሚናገሩትና ለዚህም መንግሥት በነዳጅ ላይ ሲያደርግ የነበረው ድጎማ ቀላል ግምት የሚሰጠው ባለመሆኑ ሊመሰገን ይገባል» በማለት ሀሳባቸውን ያካፈሉን የኢኮኖሚክስና የፖለቲካል ሳይንስ ባለሙያ አቶ ወሰንሰገድ አሰፋ ናቸው፡፡

እንደሳቸው ማብራሪያ፤ ምንም እንኳን በአገር ውስጥ ያለው የነዳጅ ዋጋ ከዓለም አቀፉ የነዳጅ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ቅናሽ ቢሆንም ከአገሪቷ የመክፈል አቅም ጋር ሲነጻጸር ግን አሁንም ውድ እንደሆነ ነው።መንግሥት ድጎማውን በሚያነሳበት ጊዜ ደግሞ አሁን ያለው የነዳጅ ዋጋ ውድነት በእጥፍ ሊጨምር ይችላል፡፡

የነዳጅ ዋጋ በእጥፍ በሚጨምርበት ወቅትም ነገሮች እየተካረሩ ይሄዳሉ።በከተሞች አካባቢ በተለይም ከ70 በመቶ በላይ አሽከርካሪዎች በሚገኙበት አዲስ አበባ ከተማ ላይ አሁን ካለው ከትራንስፖርት ዋጋ መናር ባለፈ የአቅርቦት እጥረትም ይታያል።ስለዚህ የነዳጅ ዋጋ ሲጨምር ለትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ማስተካከያ ካልተደረገላቸው አሽከርካሪዎች አገልግሎት የመስጠት ፍላጎታቸው ይቀንሳል።ከዚህ ባለፈም ሌሎች በዘርፉ የመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች የመግባት ዕድላቸው እየጠበበ ይመጣል፡፡

የነዳጅ ዋጋ ሲጨምር ነዳጅ ብቻውን የሚጨምር እንዳልሆነ ያነሱት አቶ ወሰንሰገድ፤ የነዳጅ ጭማሪ የተለያዩ ነገሮች ዋጋ አብሮ እንዲጨምር የማድረግ ትልቅ አቅም እንዳለው ገልጸው፤ ነዳጅ ለማንኛውም እንቅስቃሴ ወሳኝና አስፈላጊ መሆኑን ነው ያነሱት። ስለዚህ ነዳጅ ዋጋው ሲጨምር ሌሎች ምርቶችም በተመሳሳይ ዋጋቸው ይጨምራል፡፡

መንግሥት ይህን ድጎማ ሲያነሳ በተመሳሳይ ምን ላይ ሊያውለው እንዳሰበ ማንሳቱ ተገቢ እንደሆነ የገለጹት አቶ ወሰንሰገድ፤ ለአብነትም አርሶ አደሩን የሚደጉም ከሆነ ምርትና ምርታማነትን በማምጣት የምርት መጠን ከፍ ይላል።ቤቶች ልማት ላይ ካዋለውም እንዲሁ የቤት ፍላጎትና አቅርቦቱ ሊጣጣም ይችላል።ሌሎች የህብረተሰቡ መሰረታዊ ፍላጎቶች በሆኑ ዘርፎች ላይ ማዋል ከቻለና ምርት ከተትረፈረፈ የኑሮ ውድነቱን ማርገብ ይቻላል።

የነዳጅ ድጎማው መነሳት የትራንስፖርት ዋጋውን ከፍ ቢያደርገውም መንግሥት ድጎማውን አንስቶ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን ማሟላት ከቻለ ዜጎች በትራንስፖርት ያጡትን በምግብ ሸቀጦችና በሌሎች ሊያገኙት ይችላሉና ህመሙ ዘልቆ አይሰማቸው ይሆናል።ነገር ግን መንግሥት «ለነዳጅ የማወጣው ወጪ ከአቅሜ በላይ ስለሆነብኝ ነው» በማለት ገበያው ላይ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ካላደረገ የነዳጅ ዋጋ መጨመር ትልቅ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መናጋትን ይፈጥራል፡፡

ነዳጅ ትልቅ አቅም ያለው መሆኑን በመግለጽ የነዳጅ ዋጋ መጨመር በህብረተሰቡ ላይ ከሚያሳድረው ጫና ባለፈ መንግሥትንም ሊነቀንቅ እንደሚችል ያነሱት አቶ ወሰንሰገድ፤ በተለይም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማዕከል የሆነችውና ብዙ ተሽከርካሪዎች ያሉባት አዲስ አበባ ከተማ እንደመሆኗ የነዳጁ ጉዳይ በዋናነት አዲስ አበባ ከተማ ባሉት ነዋሪዎች ይበረታል።ከአዲስ አበባ ከተማ የሚነሳው የኑሮ ውድነት ደግሞ በየአካባቢው ይዳረሳል።የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ሲፈጠር ደግሞ ህገወጥነት ይበራከታል።ይህም ማህበረሰቡን ላልተገባ ወጪ የሚዳርገውና ወደ መማረር ይወስደዋል።

«መንግሥት ድጎማውን ሲያነሳ ተያይዘው ሊሰሩ የሚገባቸውን በርካታ ሥራዎች በመሥራት ህብረተሰቡ የነዳጅ ድጎማው በመነሳቱ የሚሰማው ህመም ዘልቆ እንዳይሰማው ማድረግ ይቻላል» ያሉት አቶ ወሰንሰገድ፤ ለአብነትም በግብርናው ዘርፍ ኢትዮጵያ ካላት መሬት የታረሰው እጅግ በጣም ትንሹ እንደመሆኑ በዘርፉ ሰፋፊ ሥራዎች እንዲሠሩ በማድረግ ዜጎች በቀላሉ ምግብ ማግኘት እንዲችሉና የምግብ ሸቀጦች ዋጋ እንዲቀንስ በማድረግ ማመጣጠን ይቻላል።ነገር ግን መንግሥት ድጎማውን አነስቶ ዝም ካለ ግን የሚፈጠረው ቀውስ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶክተር መንገሻ ያዮ በበኩላቸው በዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ መጨመርና በሌሎችም ምክንያቶችም ጭምር መንግሥት በነዳጅ ላይ ያደርግ የነበረውን ድጎማ ለማንሳት መገደዱን ጠቁመው፤ መንግሥት ወደዚህ ውሳኔ የመጣው የተለያዩ ጥናቶችን ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ ይናገራሉ።

ዶክተር መንገሻ መንግሥት ይህን እርምጃ ከወሰደ በኋላ ሊመጣ የሚችለውን ችግርና ይህን እርምጃ ባይወስድ ደግሞ የሚኖረውን ጫና አስመልክቶ ጥናት የተደረገ እንደሆነ ያምናሉ።አያይዘውም ምናልባትም ጫናውን መቋቋም የሚቻልበት ሌሎች አማራጮችን መውሰድ አይቻልም ወይ የሚል ጥያቄ በማንሳት፤ ድጎማው ከመነሳቱ ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችለውን የኑሮ ውድነት ከግምት ውስጥ በማስጋት ሌሎች አማራጮች መታየት የሚገባቸው እንደነበሩ አንስተዋል።

አማራጭ ካሏቸው መካካልም ድጎማውን ለማንሳት ማዘግየትም አንዱ እንደሆነ ነው ያነሱት።ይሁንና መንግሥት ድጎማውን ለማንሳት የተገደደ በመሆኑ የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲነሳ መወሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች አሉ።ምንም እንኳን በአሁን ወቅት ድጎማውን ሙሉ በሙሉ የማያነሳው ቢሆንም የቁጥጥሩ ሁኔታ አደገኛ እንደሆነና ምን ያህል ተዘጋጅቷል የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ አለበት፡፡

የቁጥጥር አቅማችን ደካማ በሆነበት አሰራር የነዳጅ ድጎማ በሚነሳበት ወቅት በአግባቡ ለማስተናገድ አዳጋች እንደሚሆን የገለጹት ዶክተር መንገሻ፤ ነዳጅ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሁሉም ዘርፎች የሚጠቀሙበት እንደመሆኑ በእያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር እንደሆነ ነው የሚገልፁት።አሁን ባለው ሁኔታም መንግሥት የዋጋ ግሽበቱን ለማረጋጋት የቱንም ያህል እርምጃ ቢወስድም የዋጋ ንረቱን መቆጣጠር አልተቻለም።አሁን ደግሞ የነዳጅ ድጎማውን በሚያነሳበት ወቅት የኑሮ ውድነቱ ይበልጥ ሊባባስና ጫናው የበለጠ ሊሆን ይችላል፡፡

በአገሪቷ አሁን ያለውን ጦርነት ጨምሮ በተለያየ ሁኔታ ህዝቡ ላይ የተፈጠረ ጫና መኖሩን አስታውሰው «የደነገጠ ማህበረሰብና የደነገጠ ኢኮኖሚ ነው ያለን» ይላሉ።በደነገጠ ኢኮኖሚና በደነገጠ ማህበረሰብ ላይ ይህን መጨመር ደግሞ ምናልባትም ኢኮኖሚው መቆጣጠር ወደማይቻልበት የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እንዳይገባ ያላቸውን ስጋት ገልጸዋል።

ስለዚህ የነዳጅ ድጎማው በሚነሳበት ወቅት የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ሙሉ ለሙሉ ማስቀረት ባይችልም የዋጋ ንረቱን መቆጣጠር የሚችልባቸውን መንገዶች በመከተል የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድና መሥራት እንደሚገባው ያነሳሉ።ለአብነትም የገበያ ስርዓቱን የስርጭትና የቁጥጥር ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል ካልቻለ የሚወሰደው እርምጃ መልሶ ችግር ፈጣሪ እንዳይሆን ስጋት አለኝ ይላሉ፡፡

የሚመጣው ችግርም ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ባይቻልም መቀነስ የሚቻልበት የፖሊሲ አማራጮችን ማቅረብ ያስፈልጋል።ከዚህ ባለፈ ግን የቁጥጥር ስርዓቱ ጠንካራ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል።

መንግሥት ለነዳጅ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ መጠን ያለው እንደመሆኑ ይህንን ወጪ አስቀርቶ ወደ ሌሎች ዘርፎች በማዋል የሚመጣው ውጤት ቀላል ግምት የሚሰጠው አለመሆኑን ጠቅሰው፤ ምርትና ምርታማነትንም ሆነ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን ማምጣት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊከወኑ የማይችሉና ረጅም ጊዜን የሚጠይቁ እንደሆኑ አንስተዋል።ስለዚህ ከነዳጅ ላይ የሚነሳው ድጎማ በግብርናውም ይሁን በሌሎች ዘርፎች አውሎ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን የወደፊት ዕቅድ ይሆን እንጂ የአጭር ጊዜ መፍትሔ ሆኖ የነዳጅ ድጎማ በመነሳቱ ምክንያት የሚከሰተውን የኑሮ ውድነት ያስቀረዋል የሚል ዕምነት የሌላቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

መንግሥት አሁን ካለበት ጫና በመነሳት በተለይም የውጭ ምንዛሪ እጥረትና ሌሎች ጫናዎችንም ጭምሮ መቋቋም እንዲያስችለው ችግሩን ማካፈል የግድ ሆኖበታል።ይሁንና በድጎማው ተጠቃሚ ያልሆነው አካል ሸክሙን መልሶ ወደ ማህበረሱ ያወርደዋል።ይህን ለመቆጣጠር ደግሞ የቁጥጥር ስርዓቱ የዳበረ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ችግሩ እንዳይባባስ ያላቸውን ስጋት አስቀምጠው፣ «መንግሥት የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ደጉሜያለሁ በሚል ዝም ማለት የለበትም።ምክንያቱም ሌሎች ላይ የተፈጠረው ጫና መልሶ ዝቅተኛ ኢኮኖሚ ባላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ሊተላለፍ ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል» ብለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ድጎማ የሚደረግበት መንገድ በራሱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ስለመሆኑም ያስረዳሉ።እርሳቸው እንደሚሉት፣ የሚደጎሙት አካላት በራሳቸው በህገወጥ መንገድ ላለመጠቀማቸው እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል በቂ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።ከቁጥጥር በተጨማሪም አማራጮችን መጠቀም የግድ ነው።ነዳጅ ከገጠር እስከ ከተማ እያንዳንዱን ዘርፍ የሚያንቀሳቅስ እንደመሆኑ የተለየ ጥንቃቄን ያስፈልገዋል።በነዳጅ ላይ የሚደረገው የፖሊሲ ለውጥም እንደማንኛውም የፖሊሲ ለውጥ መታየት የሌለበት እንደሆነም አስረድተዋል።

በነጻ ገበያ ስርዓት መንግሥት የነዳጅ ድጎማን ለምን አነሳ ብሎ ማለት የማይቻል መሆኑን ጠቅሰው፤ ነገር ግን መንግሥት ሌሎች በርካታ የማህበረሰብ ጥያቄዎችን መመለስ ያለበት ስለመሆኑ ያስረዱት አቶ ወሰንሰገድ፤ በዋናነት ዜጎች በልተው ማደር እንዲችሉ፣ ትራንስፖርት እንዲያገኙና ሌሎች መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት የመንግሥት ግዴታ መሆኑን በመግለጽ ሌሎች የማካካሻ አማራጮች ካልተወሰዱ የነዳጅ ድጎማ መነሳቱ የኑሮ ውድነቱን ሊያባብሰው እንደሚችል ነው ያስረዱት፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## መሥራት እንደ ትችት ይቅለስን!

**ዋስልኝ አየለ**

ከነገራችን በፊት፤ ይሄ ‹‹የሥራ ትንሽ የለውም›› የሚባል ነገር ግን ምነው ባስበው ባስበው አልገባህ አለኝ? አተያየቱ እንዴት ቢሆን ነው ግን? እንደአባባሉ ከሆነ እኮ በወር የመቶ ምናምን ሺ ብር ደሞዝተኛ እና የማይሸጥ ዕቃ ይዞ ጎዳና ለጎዳና ሲዞር የሚውል እኩል ናቸው ማለት ነው።ምን እንደምትሉ ልገምት! የሚያስገኘው ገቢ ማነስና መብዛት አይደለም፤ ሥራው ግን ያው ሥራ ነው ልትሉ ነው አይደል? እሺ ይሁንላችሁ!

የምር ግን የሥራ ትልቅ እና ትንሽ የለውም።ትልቅ እና ትንሽ የሚያደርገው ራሱ ባለቤቱ ነው።አንድ የሪልስቴት ባለቤት ከማስቲካ አዟሪነት የተነሳ ሊሆን ይችላል።ስለዚህ ማስቲካ ማዞርን ቀላል ሥራ አንለውም ማለት ነው።አንድ የሪልስቴት ባለቤት ካላወቀበት የዕለት ጉርሱን እስከሚያጣ ድረስ ወደ ድህነት ሊወርድ ይችላል፤ ስለዚህ የሪልስቴት ሥራም ትልቅ አይደለም ማለት ነው።ትልቅ እና ትንሽ የሚያደርገው ባለቤቱ ነው።

ከሥራ ይልቅ ‹‹ሰው እኩል አይደለም!›› ማለት ሳይቀል አይቀርም። ሰው እኩል የሚሆነው በመብት ነው፤ በትጋት ግን ይለያያል። አንዱ ሰነፍ አንዱ ጎበዝ የሆነው በልዩነት ነው።ስለዚህ የሥራ ትልቅነትና ትንሽነት በሰውየው ጥንካሬ ላይ ይወሰናል፡፡

ለማንኛውም አንድ የዓለማችን ቀላል ሥራ አለ፤ እሱም ‹‹ትችት!›› ነው።ትችት የዓለማችን ቀላሉ ሥራ ነው ብንል በፍጹም ማጋነን አይሆንም።በተለምዶ ቀላል ናቸው ከምንላቸው ሥራዎች ሁሉ ቀላል ነው።ትችት ማለት እኮ አንድ ቦታ ቁጭ ብሎ ሌሎች የሰሩትን መተቸት ማለት ነው።በነገራችን ላይ በሬዲዮም ሆነ በጋዜጣ እንደ ትችት የሚሰለቸኝ ፕሮግራም የለም(ያው እንግዲህ የግል አስታየት ነው)።

ትችት ሲባል ምክንያታዊ የሆነ ትችት እንዳለ አምናለሁ።ያ ማለት የተሰራው ሥራ በትክክልም የሚያስተች ሲሆን ማለት ነው።በሌላ በኩል የሚተቸው ሰው ያንን ድርጊት ራሱ የማያደርገው መሆን አለበት።አለበለዚያ ግን ውስጤ አምኖት አይቀበለውም።

ለምሳሌ ቆሻሻ በየመንገዱ መጣልን፣ መጥፎ ስነ ምግባርን፣ ዝሙትን፣ ሱስን... ብዙ ሰው ይተቻል።የሚያናድደው ግን ራሱ የሚያደርገውን ነገር ነው።ራሳቸው የሚያደርጉትን ነገር ሬዲዮ ላይ ወጥተው ያንኑ ድርጊት ሲኮንኑ ይሰማል።ያንን ድርጊት ይፈጽሙታልና ማበረታታት አለባቸው ወይም ዝም ማለት አለባቸው ማለት አይደለም።ዳሩ ግን መተቸት እንደመተው ቀላል አለመሆኑን ለማሳየት ነው።ያ ስለዝሙትና ስለስካር ሲያወግዝ የነበረው ጋዜጠኛ ራስህ ተወው ቢባል ላይተወው ይችላል፤ መተቸቱ ግን ቀላል ስለሆነ በየዕለቱ ያብጠለጥላል፡፡

ብዙ ጊዜ ማህበራዊ ሚዲያም ሆነ ዋናዎቹ ሚዲያዎች ላይ የምንታዘበው ነገር አለ።በተለይም በአርቲስቶች ጎራ (ብዙ ጊዜ ወጣ ያለ ነገር የሚታየው ከዚያ ስለሆነ) አንድ ነገር ሲፈጠር ሰዎች ጎራ ፈጥረው ይከራከራሉ። ለምሳሌ ድርጊቱ ነውር ከሚባሉ ነገሮች (ዝሙት፣ ራቁት) ቢሆን፤ ድርጊቱን የሚኮንኑ እንዳሉ ሁሉ ‹‹ደግ አደረገ/ች የሚሉም አሉ።

‹‹ደግ አደረገ/ች›› የሚሉ ሰዎች ምክንያታቸው፤ ‹‹ሁላችንም ስላልተያዝን ነው እንጂ እናደርገዋለን›› በማለት ነው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ነውረኝነትን ከቁጣ ጋር ያወግዙታል።

ይህ የሆነው እንግዲህ፤ ሁሉም የመሰለውን የተናገረ መተቸት ቀላል ስለሆነ ነው።እነዚያ ሲያወግዙ የነበሩት ሰዎች በትዳራቸው ላይ የሚወሰልቱ ሊሆኑ ይችላሉ።ያወገዙት/ዟት ዕለት ማታ ራሱ ከትዳራቸው ውጭ ሊወሰልቱ ይችላሉ፡፡

አንድ ነገር ግን ያስማማናል! በማሕበረሰቡ ዘንድ ነውር የሆነ ነገር ሲከሰት ‹‹እኔም አድርጌዋለሁና አልተችም›› አይባልም።ባንተች እንኳን የድርጊቱን ባለቤት የተቹትን ልናወግዝም አይገባም።

የትችት ነገር ሲነሳ፤ ብዙ ጊዜ በቀልድም ይሁን በቁም ነገር አንድ የሚጠቀስ ማሳያ አለ። ሲጋራ የሚያጨስ መምህር ስለሲጋራ ጉዳት ቢያስተምር ተማሪዎች እንዴት ይቀበሉታል የሚል ነገር ይነሳል(ለነገሩ ሲጋራው ራሱ ለጤና ጎጂ መሆኑን በማሸጊያው ላይ ይናገራል)።

ራሱ መተው ያልቻለውን እንዴት ለሌሎች ጎጂ ነው ብሎ ያስተምራል ለማለት ተፈልጎ ነው።

ሲጋራ የሚያጨስ መምህር ስለሲጋራ ጎጂነት ድብን አድርጎ ማስተማርና መምከር ይችላል! እሱ መተው አልቻለም ማለት ሌሎችም አይችሉም ማለት አይደለም።እሱ መተው ባለመቻሉ ደካማነቱን እየገለጸ ያለውን አስከፊ ጉዳት መናገሩ እንዲያውም ከማያጨሱት የበለጠ አሳማኝ ይሆናል።ይሄ ሰው እኔ እያጨስኩ እንዴት ስለሲጋራ ጎጂነት እመክራለሁ ማለት የለበትም! ቢችል መተው፤ ካልቻለ ግን ሌሎች እንዳያጨሱ መምከር!

ስለዚህ ይህን መምህር መተቸት የለብንም ማለት ነው።መተቸት ቀላል ስለሆነ ነው የተቸነው።ይሄኔ እኛም ከእሱ የባሰ መተው ያልቻልነው መጥፎ ልማድ ይኖር ይሆናል።ትችት የሚገነባውና የሚያንጸው ነገር እንዳለ ሁሉ ነባራዊ ሁኔታውን ያላገናዘበ ከሆነ ግን ተቺውን ራሱን ትችት ላይ ይጥለዋል።

ገጠር ውስጥ ቤተክርስቲያን ቄሶች ሲሰብኩ አንድ የምሰማው ነገር ነበር።‹‹ቄስ ሲሰክር አየን ብላችሁ አትስከሩ፣ ቄስ ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ሲወሰልት አየን ብላችሁ አትወስልቱ፤ በምድርም በሰማይም የሚዋረደው ራሱ ነው›› ይሉ ነበር።

እርግጥ ነው አርዓያ ሆኖ መገኘት ምንም አያከራክርም! ያ ካልሆነ ግን ያ ሰው መምከር የለበትም ማለት አይደለም።በራስ መተማመን ካለን ከሰውየው የምንወስደው ሳይንሳዊ እውነታውን ነው።በነገራችን ላይ ‹‹እገሌ ራሱ ያደርገው የለ እንዴ!›› የምንለውም ትችት ቀላል ስለሆነ ነው።እኛ ልናደርገው ስንፈልግ ነው በእሱ የምናሳብበው።

እደግመዋለሁ! ትችት አያስፈልግም እያልኩ አይደለም።ዳሩ ግን እኛው ራሳችን የምናጠፋውን ጥፋት ሰዎች ላይ ሲሆን ንፁህ መስለን መተቸት ስንፍና ነው።በሌላ በኩል ደግሞ ከመተቸታችን በፊት የነገሩን ነባራዊ ሁኔታ ማጤን ይጠበቅብናል።

ከምንም በላይ ትችት ቀላል መሆኑን የምናረጋግጠው ግን በየመድረኩ የሚነገሩ ነገሮች ናቸው።ለምሳሌ አንዱ የሚገርመኝ የሰዓት አጠቃቀም ነው።ሁለት ሰዓት ተኩል የተባለ ስብሰባ ሦስት ወይም አራት ሰዓት ይመጣና ከእሱ በኋላ የመጡ ሰዎችን ይተቻል።‹‹ሐበሻ ስንባል መቼ ይሆን የምንሰለጥነው!›› እያለ ይናደዳል።ይሄን ማለት ቀላል ነው፤ ልክ በተባለው ሰዓት መድረስ ግን ከባድ ነው፡፡

ቆሻሻ በየመንገዱ የሚጥሉ ሰዎችን መስደብና መውቀስ ቀላል ነው፤ ቆሻሻ ማጽዳት ግን ከባድ ነው።ማጽዳት ቀርቶ አለመጣል ራሱ በተገባ ነበር፤ ግን እየጣልን ነው የጣሉትን የምንተቸው።

በተቻለን መጠን እንዳይደረጉ የምንፈልጋቸውንና የምንመክራቸውን ነገሮች ራሳችንም ባናደርግ! ከዚያ ውጭ ደግሞ የምንተቻቸውን ነገሮች መሰረታዊ ምክንያታቸውን ብናጤን! ካልሆነ ልማዳቸው ነው እየተባልን ነው የምንታለፈው!

ምክንያታዊ እንሁን! እንዲደረጉ የምንፈልጋቸውን ነገሮች ራሳችን እናድርግ!

# ዓለም አቀፍ

## በቴክሳስ አንድ የጭነት መኪና ውስጥ ቢያንስ 40 ሰዎች ሞተው ተገኙ



በሳን አንቶኒዮ ቴክሳስ ግዛት ወጣ ብሎ በሚገኝ ስፍራ አንድ የጭነት መኪና ውስጥ ስደተኞች እንደሆኑ የታመኑ ቢያንስ 46 ሰዎች ሞተው ተገኙ። በሕይወት የተረፉ አራት ህጻናትን ጨምሮ 16 ሰዎች ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸውን አንድ የእሳት አደጋ ባለሥልጣን ተናግረዋል።

በሕይወት የተረፉ ሰዎች ሰውነታቸው በሙቀት ግሎ እንደነበርና በከፍተኛ ሁኔታም መዛል ታይቶባቸዋል ተብሏል። ከአሜሪካ እና ሜክሲኮ ድንበር 250 ኪሎሜትር ላይ የምትገኘው የሳን አንቶኒዮ ከተማ ለህገወጥ ሰዎች አዘዋዋሪዎች ዋና መተላለፊያ ናት።

ወደ አሜሪካ መሻገር የቻሉ ሰነድ የሌላቸው ስደተኞችን ለማጓጓዝ ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች የጭነት መኪኖችን ይጠቀማሉ። “የሞቱት ሰዎች ቤተሰብ አላቸው። የተሻለ ሕይወት ለማግኘትም ይሆናል ወደዚህ የመጡት። አሰቃቂ የሰብአዊ ሁኔታ ነው” በማለት የሳን አንቶኒዮ ከንቲባ ሮን ኒረንበርግ ተናግረዋል።

የሳን አንቶኒዮ የእሳት አደጋ መከላከያ አዛዥ ቻርለስ ሁድ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎች መጀመሪያ ወደ ስፍራው የደረሱት በአገሬው ሰዓት አቆጣጠር 12 ሰዓት ከምሽቱ ነው። “የጭነት መኪናውን በር ከፍተን ስናይ እንዲህ የተደራረቡ አስከሬን እናያለን ብለን መቼም አልጠበቅንም። ማናችንም ብንሆን ያንን አስበን ወደ ሥራ አንመጣም” ብለዋል ።

አሽከርካሪ የሌለው የጭነት መኪና ምንም አይነት የአየር ማቀዝቀዣ እንዲሁም ለመጠጥም የሚሆን እንዳልነበረው አክለዋል። የሜክሲኮ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማርሴሎ ኢብራርድ ወደ ሆስፒታል ከተወሰዱት መካከል ሁለት ጓቲማላውያን ይገኙበታል ብለዋል። የሌሎቹ ተጎጂዎች ዜግነት እስካሁን አልተገለጸም። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሶስት ሰዎች በእስር ላይ ሲሆኑ ምርመራውም ለፌዴራሉ ፖሊሶች መተላለፉን ቢቢሲ ዘግቧል።

## በማላዊ በአልቢኖ ግድያ ወንድሙ እና ቄስን ጨምሮ አምስት ሰዎች በእስር ተቀጡ



በማላዊ የአካል ክፍሎቹን ለመሸጥ ያቀዱትን አልቢኖ በመግደል ወንጀል የተከሰሱ አምስት ሰዎች የዕድሜ ልክ እስራት ከከባድ የጉልበት ሥራ ጋር ተወሰነባቸው። ማክዶናልድ ማሱምቡካ አልቢኒዝም (በተፈጥሮ ቆዳ፣ ዓይን እና ጸጉርን ነጭ የሚያድርግ ክስተት) የነበረበት ሲሆን የተገደለውም በአውሮፓውያኑ በ2018 ነበር። የዕድሜ ልክ ቅጣት ከተላለፈባቸው መካከል አንዱ የማሱምቡካ ወንድም ነው።

አልቢኖዎችን መግደል ከጥንቆላ ሥነ ሥርዓቶች ጋር የተቆራኘ ነው። አልቢኒዝም ያለባቸው ሰዎች መልካም ዕድል ያመጣሉ የሚል የተሳሳተ እምነት በስፋት ይታያል። በማላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማክሰኞ ዕለት ፍርድ ከተላለፈባቸው መካከል የካቶሊክ ቄስ የሆኑት ቶማስ ሙሆሻ ናቸው። ቄስ ሙሆሻ ከሌሎች አራት ሰዎች ጋር የ30 ዓመት እስራት ተከናንበዋል።

ውሳኔውን ያስተላለፉት ዳኛ ዶርቲ ኒያካውንዳ ካማንጋ በቅጣቱ ዙሪያ ከግምት ካስገባቻቸው ምክንያቶች መካከል ሟቹ በቅርብ ሰዎች መከዳቱን፣ ግድያው በጥንቃቄ የታሰበበት እና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ መገደሉን መሆኑን ጠቁመዋል። እአአ በ2018 ካህኑ በግድያው መሳተፋን የሚገልጽ ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ ከተሰማ በኋላ የማላዊ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሙሆሻን ከክህነት አግዶታል።


ባለፉት አስር ዓመታት ማላዊ በአልቢኖዎች ላይ ያነጣጠረ ተደጋጋሚ ጥቃት አስተናግዳለች። አጥንቶቻቸው እና የአካል ክፍሎቻቸው ሀብትን ወይም መልካም ዕድልን ጠያመጣል በሚል ነው የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት። እንደ ኦፊሴላዊ አሃዝ ከሆነ ከ 2014 ጀምሮ በአልቢኒዝም ጋር የሚኖሩ ከ 170 በላይ ሰዎች በተመሳሳይ ጥቃቶች ተገድለዋል ወይም ተጎድተዋል ሲል የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ዜን ሴክሬታሪ ሺመላሽ በቀለ (1921 – 2001 ዓ.ም)

**ግርማ መንግሥቴ**



ላለፉት ሳምንታት ከዛሬው ባለውለታችን ብዙም ባልራቀ መልኩ ለአገር ያገለገሉ፤ በስራቸው ህያው የሆኑ ሰዎችን አንስተን ባለውለታነታቸውን ዘክረናል። ከልደት እስከ ሕይወት ፍፃሜያቸው ያከናወኑትን እየጠቀስን ገጻችን የቻለችውን ያህል ዘርዝረንላቸዋል፤ ወደ አሁኑ ትውልድ ይመጡ ዘንድም አድርገናል። ዛሬም ከብዕር ባለፈም፣ በጊዜና እውቀታቸው፤ አገራቸውን ያገለገሉ ባለውለታን ይዘን መጥተናል። ዜን ሴክረታሪ ሺመላሽ በቀለን።

አቶ ሺመላሽ በቀለ ከአባታቸው ከደጃዝማች በቀለ ለሙ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዝማምነሽ ወልደ የሱስ በቀድሞ ስሙ ጎጃም ክፍለ አገር፣ ሜጫ አውራጃ፣ ልዩ ስሙ ደጋ እቦሌ በተባለው ሥፍራ በ1921 ዓ.ም ተወለዱ።

ከቀኛዝማች ለሙ ኃይሉ የሚወለዱት፣ የአቶ ሺመላሽ አባት ደጃዝማች በቀለ ለሙ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በይፋ በወረረችበት ወቅት አገር የማዳን ኃላፊነትን ወስደው ከአርበኞች ጋር ተሰልፈው ላደረጉት ተጋድሎ፣ ለፈፀሙት ጀብድና ላበረከቱት የአርበኝነት ተግባር ከፊታውራሪነት ወደ ደጃዝማችነት በማደግ ማእረጉን ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ ተቀብለዋል፤ የአምስቱን ዓመት የአርበኛ ሜዳይ፤ ሁለት የክብር ኮከብ (Grand Officer's)፤ የቀ.ኃ.ሥ ኒሻንና የድል ኮኮብ ሽልማትንም አግኝተዋል። ይህ የሺመላሽ አባት የአርበኝነት ሕይወት ለሺመላሽም ስንቅ ሆኖ አገልግሏል።

በዚህ የአርበኝነት ዘመን ሺመላሽ ገና በሰባት ዓመት ለጋ ዕድሜው ከአባቱ ጎን ተሰልፎ ለሰራዊቱ ግብዓት በማመላለስ፤ አስፈላጊ በሆነበት ሥፍራ ሁሉ የአርበኞችን መልዕክት ካለፍርሃት ሲያደርስ ቆይቷል። ለዚህ ተግባሩም ከመንግስት ሽልማቶችን አግኝቷል። ይህም ገና በልጅነቱ ከፍተኛ የአገር ፍቅር ስሜትና አርበኛነትን በውስጡ እንዲያሰርፅ ያደረገው መሆኑን ነው አፈላልገን ያገኘናቸው ልጃቸው አቶ አስፋወሰን ሺመላሽ የነገሩን።

ይህንን በዓርአያነት የተረከበው ወጣት ሺመላሽ በነበረው ውስብስብ ሕይወት እና የአስተዳደግ ተሞክሮ ሳይበገር ዕድሜው የፈቀደለትን ሁሉ በማድረግ በዘመኑ ይሰጥ ከነበረው የሃይማኖት ትምህርት መንፈሳዊ እውቀትን መቅሰም በመቻሉ የመጀመሪያ ደረጃ ክህነትን አግኝቷል። በመቀጠልም በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ በተገኘ ዕድል በአዳሪ ትምሕርት ቤት የዘመናዊ ትምሕርት እንዲያገኙ ከተሰጣቸው ጥቂት ወጣቶች አንዱ ለመሆን በቅቶ የመጀመሪያ ደረጃ ትምሕርቱን ተከታትሏል።

በጀነራል ዊንጌት የጽሕፈት /አካዳሚክስ/ ትምህርታቸውን በመከታተል በውጤት ያጠናቀቁት አቶ ሺመላሽ በቀለ በዘመኑ በገንዘብ ሚኒስቴር፤ በኢትዮጵያ አየር መንገድ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተለያዩ ዘርፎች አገልግለዋል።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ በ1947 ዓ.ም ሐምሌ ወር በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአውቶሚክ ኃይልን ለሠላማዊ አገልግሎት ለማዋል በጀኔቭ (ስዊትዘርላንድ) በነበረው ታላቅ ዓለም አቀፍ ጉባዔ ላይ እንዲገኙ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥት መልዕክተኞች ዋና ፀሐፊ በመሆን በጉባዔው ላይ ለመካፈል ችለዋል። በአጋጣሚው የተባበሩት መንግሥታት ሴክሬታሪ ጀነራል ከነበሩት ከሚስተር ዳግ ሃመርሾልድ ጋር ለመተዋወቅና ስለሀገራቸውም ለመወያየት ዕድል አግኝተዋል። በኋላም ካሪየር ዲፕሎማት ሆነው በመሾማቸው የተለያየዩ በርካታ የአለም አገራት በመዞር በከፍተኛ ኃላፊነት የኢትዮጵያን ጉዳይ ማስፈጸም፣ መፈጸምና በዲፕሎማሲው መስክ የአገራቸውን ጥቅም ማስከበር መቻላቸውን አቶ አስፋውና የተገኙት የፅሁፍ መረጃዎች ያመለክታሉ። በየሄዱባቸው አገራት ከየአገራቱ መሪዎችና ዲፕሎማቶች ጋር የተነሷቸው፤ በአቶ አስፋው በኩል የተመለከትናቸው የተለያዩ ታሪካዊ ፎቶግራፎችም ይህንኑ ይመሰክራሉ።

አቶ ሺመላሽ በኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር በአሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ዜን ሴክሬታሪ በመሆን ተሹመው ከስምንት ተኩል ዓመታት በላይ ተግባራቸውን በትጋት ተወጥተዋል። በዚህ ዕድል በመጠቀም የነበራቸውን ትርፍ ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም ራሳቸውን በትምሕርት ለማነፅ በአሜሪካ፣ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው አሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲ እና የዓለም አቀፍ ሕግ ትምሕርታቸውን ለመከታተል ችለዋል። አቶ ስሜነህ የተባሉ ጸሐፊም "በ1950 ዓ.ም ሺመላሽ በቀለ በአሜሪካን አገር በኢትዮጵያ መንግሥት ኤምባሲ፣ በጸሐፊነት ተሹሞ ከተላከ በኋላ አስደሳች ሥራዎችን በትጋትና በቅልጥፍና በመሥራት ተመስጋኝ ሆኖ ነበር።" (ስሜነህ፤ ገጽ 72፣ 2007 ዓ.ም) በማለት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

አቶ ሺመላሽ በቀለ የዲፕሎማሲ ሥራቸው ስኬት በፈጠረው መነቃቃት የበርካታ አገሮችን የአኗኗር ዘይቤ፤ ባህልና የአስተዳደር ፈሊጥ ልቅም አድርገው ለመቅሰምና ለመገንዘብ ሰፊ ዕድል እንዳገኙ እና የዲፕሎማሲ ሥራ የአስተሳሰብ እና የአመለካከት ለውጥን ጨምሮ ለዕውቀት መዳበር በእጅግ እንደረዳቸው በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ያጫውቱኝ ነበር ያሉት አቶ አስፋወሰን፤ በዚህ አጋጣሚ ተወዳጁን የአሜሪካ ፕሬዚደንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ እና የወቅቱ የአሜሪካ ሱፕሪም ኮርት አቶርኔ ጀነራል የነበሩትን ሮበርት ኬኔዲን ለመተዋወቅ እና በአገራቸው ጉዳይ ላይ ለመታደም ትልቅ አጋጣሚና ዕድል ከተጎናጸፉት ሰዎች መካከል አንዱ መሆን መቻላቸውንም ነግረውናል።

በአውሮፓ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በኤዥያ በነበራቸው የሥራ ጉብኝት የእስራኤሏን ዝነኛ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚስ ጎልዳማየርን ጨምሮ በወቅቱ ከነበሩት ከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸው ጋር የመገናኘት ዕድሉንም አግኝተዋል። አቶ ሺመላሽ በቀለ በዲፕሎማሲ ሥራቸው በወቅቱ ነፃ የወጡና በመውጣት ላይ የነበሩ የአፍሪቃ አገራት መሪዎችንም በስፋት አግኝተው መወያየት የቻሉ ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማት ነበሩ።

በተለይም የኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትና በኋላም በሰው እጅ ሕይወታቸው ያለፈው ፓትሪስ ኤመሪ ሉሙምባ የቅርብ ወዳጃቸው እንደነበሩም ከታሪካቸው መረዳት ተችሏል። በመጨረሻም በሕግ መወሰኛ ም/ቤት የፕሬስ የጥናትና የፐብሊክ ሪሌሽን ዳይሬክተር በመሆን ማገልገል ችለዋል።

በአገር ውስጥ ከቀድሞ የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ፤ የቀድሞ አዲስ አበባ የባለአደራ ምክር ቤት ከንቲባ የነበሩት ክቡር ኢንጂነየር ብርሃነ ደሬሳ ጋር በአሜሪካን አገር በኢትዮጵያ ኤምባሲ አብሮ የመሥራት ዕድል አግኝተዋል። እጅግ በጣም የቅርብ ወዳጅ እና ጓደኞቻቸው ከነበሩት ውስጥ የክብር ዶክተር አቶ አለ ፈለገሰላም፤ ዕውቁ ደራሲ አቶ አቤ ጉበኛ፤ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት፤ አቶ ዓለማየሁ ሞገስ፤ አቶ ማሞ ውድነህ ... ጥቂቶቹ ናቸው። በሌላ በኩል ከክቡር ም/ጠ/ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፤ ክቡር አቶ ዮሴፍ ረታና ከክቡር አቶ አያሌው ጎበዜ የቀድሞው የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደሮች ጋርም ትውውቅ የነበራቸው ሲሆን፤ ተገናኝቶም በአገራዊ ጉዳይ ላይ ሀሳብ የመለዋወጥ እድል እንደነበራቸው አቶ አስፋው ይናገራሉ።

አቶ ሺመላሽ በቀለ የአስተዳደጋቸው ሁኔታ ከመካከለኛ ቤተሰብ መሆናቸው እንደመታወቁ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አስተዳደር በግል የደረሰባቸው የከፋ ችግር አልነበረም፤ ሆኖም በኢትዮጵያ ፍትሕ እና ርትዕ ጠፍቷል፤ አስተዳደርም ተዛብቷል፤ ሕጉም ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም በሚል እምነት አድልዎን እና ፍትህ አልበኝነትን ለማስወገድ አመፅን እንደዋነኛ የትግል ስልት ለመጠቀም ሞክረዋል።

ከባላምባራስ አሸብር ገ/ሕይወት፤ ከአፈንጉሥ ታከለ ወ/ሐዋርያት፤ ከደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ፤ ከጀነራል ታደሰ ብሩ፤ እና ሌሎችም ጋር በምሥጢር በመቀላቀል በወቅቱ ወገናቸውን ለመርዳት እና በንጉሠ ነገሥቱ መንግስት የአገዛዝ ሥርዓት የነበረውን ከፍተኛ የፍትህ ግድፈት ለማረም እንዲቻል በግልፅና በህቡዕ ትግል ከታናሽ ወንድማቸው ከአቶ ስሜነህ በቀለ ጋር በመሆን በመሳተፋቸው ለተደጋጋሚ ግዞት እስራትና እንግልት ደርሶባቸዋል።

በዚሁ ምክንያት ለእስር ተዳርገዋል። በብዙ ትግል ከእስር የተፈቱ ቢሆንም፤ ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ በተፈቀደላቸው ሥፍራ፣ በባሕር ዳር ከተማ እንደግለሰብ በግዞት እንዲቆዩ ሲደረግ፤ በወቅቱ በየዕለቱ ጠዋት፣ በሥራ ሰዓትና ከሰዓት በኋላ በሥራ መውጫ ሰዓት በተዘጋጀላቸው የመቆጣጠሪያ መዝገብ ላይ እየፈረሙ ካለሥራ እንዲኖሩ ሲወሰንባቸው በግል ሥራ ካልሆነ በስተቀር በአገር ውስጥ በማንኛውም የመንግሥት ሥራ ተቀጥረው እንዳይሠሩ፤ ወደ ውጭ አገርም እንዳይወጡ በንጉሱ ውሣኔ ተላልፎባቸው ቆይቷል።

ይህ ውሣኔ የደርግ መንግሥት አገሪቷን እስከተቆጣጠረበት 1967 ዓ.ም ድረስ እንኳን ፊርማው የተቋረጠ አልነበረም። ለዚህ እስራትና ግዞት የዳረጋቸው ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ከተከበሩ አፈንጉስ ታከለ ወ/ኃዋርያት ጋር ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ለመግደል እና የንጉሰነገሥቱን መንግሥት ለመገልበጥ አሲረሃል በሚል ሲሆን፤ ከሞት ቅጣት ለመትረፍና ሕይወታቸውን ለማቆየት የቻሉት በአባታቸው በደጃዝማች በቀለ ለሙ አገራዊ ውለታና ጥረት መሠረት መሆኑም ይነገራል።

የዚህ ከፍተኛ እና የረቀቀ የትግል ታሪክ አቶ በሪሁን ከበደ በ"የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ታሪክ" መጽሐፋቸው (ገጽ 710-765፤ 1993 ዓ.ም)፣ "አያሌው መንግሥት" በሚል ርዕስ በራሳቸው በአቶ ሺመላሽ በቀለ እጅ እንዲሰፍር ሆኖ መዘጋጀቱን፤ ደራሲው ከዚህ አለም በመለየታቸው ምክንያት መዘግየቱንና የጎደሉ መረጃዎች ተሟልተው በቅርቡም ለህትመት እንደሚበቃ አቶ አስፋው ነግረውናል።

በዚህ አጋጣሚ አቶ ሺመላሽ በቀለ "ደስታ ጭቃ ነው"፤ "ሮስተም" እና "ሶኸራብ" የሚሉትን ልብ ወለድ እና የግጥም መድበል፤ እንዲሁም "የኢራን ዘውድ ዐምድ" መጽሐፍ በስድሳዎቹ ውስጥ ለህትመት ያበቁ ደራሲም እንደነበሩ መገንዘብ ተችሏል። ከነዚህ በተጨማሪ "ከጥንት እስከዛሬ"፤ "እንስሳም እንደሰው"፤ "ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና ታሪካቸው"፤ "መካኒቱ አገሬ"፤ "የዲሞክራሲ ምሥጢር"፤ "ዐባይ እና ጣና"፤ "የዓለም ጉዞ"፤ "ናስቲለው"፤ "የባሕር ዳር ከተማ ታሪክ" ወዘተ የሚሉት በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ መጻሕፍት እንዳላቸው ከቤተሰቦቻቸው የተገኘው ማስረጃ የሚያመለክት ሲሆን፤ በወንድማቸው በአቶ ስሜነህ በቀለ መጽሐፍ (ገጽ 225-2007) ላይም ይኸው ተረጋግጦ ይገኛል።

ይህ ብቻም አይደለም፤ "...በወቅቱ የተነደፈው ስትራቴጂ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ሥነ-ሥርዓት በኋላ ምን ጊዜም ወደ ፓርላማ አዳራሽ የሚያመሩት [ቀ.ኃ.ሥ.] በግልጥ መኪና ላይ ተቀምጠው ስለሆነ በባለ መነፅር ጠመንጃ እንደ ፕሬዚዳንት ኬኔዲ አገዳደል ሁሉ ጥይቷን ከርቀት አነጣጥሮ ተኩሶ በመምታት መፈጸም እንዲቻል መሣሪያውን የሰጡን ሜጀር ጀነራል ጃጋማ ኬሎ ሲሆኑ የተረከበው ግን ልጅ ሺመላሽ በቀለ እንደነበር [...]" (ስሜነህ፤ በገጽ 95፤ 2007) የሚል የዜን ሴክሬታሪ ሺመላሽ በቀለ ታሪክ ሰፍሮ ይገኛል።

አቶ ሺመላሽ በቀለ በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ታስረዋል፤ በደርግ መንግሥትም ራሳቸው መንግስቱ ኃይለማሪያም በተገኙበት "የዓሣ ግማቱ ..." በሚለው ንግግራቸው ከመታሰራቸውም በላይ፤ በ1982 ዓ.ም ኢሕአዴግ ባሕርዳር ከተማን በተቆጣጠረበት ጊዜም "መጤ ገዥዎቼን" አልቀበልም ሲሉ በማመጻቸው ከስምንት ወራት ተኩል በላይ ወደ ወህኒ ወርደው እንደነበርም ታሪካቸው ያስረዳል። አቶ ሺመላሽ በቀለ ከሕግ ሚስታቸው ሁለት ሴቶችንና አንድ ወንድ ልጅ ያፈሩ ሲሆን፤ ባደረባቸው ከፍተኛ የካንሰር ህመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ጥቅምት 5 ቀን 2001 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው አስከሬናቸው በባሕርዳር ቅ/ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ዘመድ ወዳጆቻቸው በተገኙበት ከታዋቂው አርበኛ ከደጃዝማች አበረ ይማም መቃብር ጎን በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል።

**ይህንን ጽሑፍ ስናጠናቅር በቃል ካነጋገርናቸው ሰዎች በተጨማሪ፤**


1. ስሜነህ በቀለ ለሙ፤ "የታላቁ አመፅ ምስጢር እና አጭር የቤተሰብ ታሪክ"፤ 2007፣ ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፤
2. በሪሁን ከበደ፤ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ፤ መስከረም 21 ቀን 1993 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፤
3. የኢትዮጵያ ፓርላሜንት መጽሔት ዓመታዊ መግለጫ ጥቅምት 23 - ሐምሌ 1 1958፤ ቁ. 7 በፓርላሜንቱ ማስታወቂያ ክፍል የተዘጋጀ አዲስ አበባ፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፤
4. International Atomic Energy Agency, Atomic Energy for Peace the First International Summit August 1955.


በምንጭነት መጠቀማችንን እንገልፃለን።

# ስፖርት



## የፕሪሚየርሊጉ ዋንጫ አሸናፊ የመጨረሻ ፍጥጫ

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ በ1990 እንደ አዲስ መካሄድ ከጀመረ ወዲህ እንደ ዘንድሮው የውድድር ዓመት መጨረሻው እጅግ አጓጊና ጣፍጭ የሆነበት አጋጣሚ በቅርብ ዓመታት ታይቶ አያውቅም። ከመጀመሪያው አንስቶ የቻምፒዮንነት ጉዞው የአንድ ክለብ ግልቢያ የመሰለው የ2014 ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ የማታ ማታ ከሃያ ሳምንት መርሃግብር ጨዋታዎች በኋላ ቀድሞ ከነበሩ ግምቶች ተቃራኒ የሆኑ ውጤቶች እየተመዘገቡበት ሄደዋል። ይህም ትልቁን ዋንጫ የመሳም እድሉ ወደ አንድ ክለብ ብቻ እንዳያዘነብል አድርጎ የሊጉን የመጨረሻ ጨዋታዎች በጉጉት የተሞላ አድርጎታል።

የሊጉ ያለፉ አምስትና ከዚያ በላይ ሳምንታት ጨዋታዎች ከመጀመሪያ አንስቶ በሰፊ የነጥብ ልዩነት እየመራ የነበረው ቅዱስ ጊዮርጊስና በተከታዩ ፋሲል ከነማ መካከል ፉክክሩ እየጦዘ መጨረሻው ሳምንት መርሃግብር ድረስ ዘልቋል። የመጨረሻውና ሰላሳኛው ሳምንት መርሃግብር ጨዋታዎች ከነገ ጀምሮ በባህርዳር ስቴድየም ሲካሄዱም ፈረሰኞቹና አጼዎቹ ዋንጫውን የማንሳት ተስፋቸውን ይዘው ወደ ሜዳ ይገባሉ።

የዓምና የሊጉ ቻምፒዮን አጼዎቹ በታሪካቸው ሁለተኛውን ዋንጫ ለመሳም አጀማመራቸው ደካማ ቢመስልም ከሊጉ አጋማሽ በኋላ አስደናቂና ስኬታማ ጉዞ አድርገው ከፈረሰኞቹ ጋር የነበራቸውን ሰፊ የነጥብ ልዩነት ወደ አንድ በማጥበብ የቻምፒዮንነት ፉክክሩ አጓጊ እንዲሆን ነብስ ዘርተውበታል። ፈረሰኞቹ በአንጻሩ ለረጅም ሳምንታት መሪነታቸውን አስጠብቀው ቢጓዙም በአጼዎቹ የደረሰባቸው የመጀመሪያ ሽንፈትና በተደጋጋሚ ነጥብ መጣላቸው ለአስራ አምስተኛ ጊዜ ዋንጫውን ለማንሳት የነገውን የመጨረሻ መርሃግብር እንዲጠብቁ አስገድዷቸዋል። ያምሆኖ የቻምፒዮንነት እድላቸው በአንድ ነጥብ ልዩነት ከሚከተሏቸው አጼዎቹ የተሻለ ሆኖ ለነገው ወሳኝ ፍልሚያ አድርሷቸዋል። ፈረሰኞቹ ዋንጫውን ለመሳም በነገው የመጨረሻ ፍልሚያ አዲስ አበባ ከተማን የማሸነፍ ግዴታ ውስጥ ገብተው ይገጥማሉ። ከማሸነፍ ውጪ የአቻ ውጤት እንኳን ፈረሰኞቹ ዋንጫውን ለማንሳት አያዋጣቸውም። በአንጻሩ አጼዎቹ የፈረሰኞቹን ነጥብ መጣል እየተጠባበቁ ከሊጉ ላለመውረድ የሚጥረው ድሬዳዋ ከተማን በነገው ፍልሚያ ማሸነፍ ብቻ የዋንጫ ተስፋቸው ይሆናል።

የሊጉ ዋንጫ ከሁለቱ ብርቱ ተፎካካሪዎች በአንዱ እጅ መግባቱ እርግጥ ነው። ይህም በቀጣዩ ዓመት ኢትዮጵያን ወክለው በአፍሪካ ታላላቅ ውድድሮች የሚካፈሉበትን እድል ቀድመው እጃቸው እንዲያስገቡ አድርጓቸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘም ካፍ የአፍሪካን ታላላቅ የክለቦች ውድድሮችን በተመለከተ የክለቦችና የተጫዋቾች ምዝገባ እንዲሁም የውድድሮቹን ቀናት መረጃዎች ይፋ አድርጓል።

የአፍሪካ ቻምፒየንስ ሊግና ኮንፌዴሬሽን ካፕ በየአመቱ የአገራት የሊግ አሸናፊዎችና ሁለተኛ የወጡ እንዲሁም የጥሎ ማለፍ ባለድሎችን እንደየአገራቱ የውስጥ ሊግ ህጎች እያሳተፈ እንደሚገኝ ይታወቃል። ከኢትዮጵያም በየትኛው ውድድድ የትኛው ክለብ እንደሚሳተፍ ነገ የሚለይ ቢሆንም ቅዱስ ጊዮርጊስና ፋሲል ከነማ ነገ የሚጠብቃቸው ፍልሚያ ለሊጉ ቻምፒዮንነት ብቻ ሳይሆን በትልቁ የአፍሪካ ቻምፒዮንስሊግ ለመሳተፍ ጭምር የሚዋደቁበት ሆኗል። የሊጉን ዋንጫ የሚያነሳው ወደ አፍሪካ ቻምፒዮንስ ሊግ ያመራል። ሁለተኛ ሆኖ የሚያጠናቅቀውም የአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ላይ የሚሳተፍ ይሆናል።

ካፍ የ2022/23 አህጉራዊውን ፍልሚያ በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎችን ከቀናት በፊት ይፋ ያደረገ ሲሆን፣ በሁለቱም ውድድሮች ላይ የሚሳተፉ ክለቦችን ብሔራዊ ፌዴሬሽኖች የሚያስታውቁበት ቀን ወደ ሐምሌ 24 (ጁላይ 31) መገፋቱ ተረጋግጧል። በመጀመሪያ የቅድመ ማጣሪያ ዙር የሚካፈሉ ክለቦች የሚጠቀሙባቸውን ተጫዋቾች የሚያስገቡበት ቀን ደግሞ ከሐምሌ 25-ነሐሴ 9 ድረስ መሆኑ ተጠቁሟል።

በካፍ የክለቦች ውድድር ደረጃ የመጀመሪያ 12 ቦታዎችን የያዙት አልጄሪያ፣ አንጎላ፣ ዲ አር ኮንጎ፣ ግብፅ፣ ጊኒ፣ ሊቢያ፣ ሞሮኮ፣ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ እና ቱኒዚያ በሁለቱም ውድድሮች ሁለት ሁለት ተሳታፊ ክለቦችን እንደሚወክሉ ይታወቃል። ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎቹ ሀገራት ግን እንደየደረጃቸው ከመጀመሪያ የቅድመ ማጣሪያ ጀምሮ ጨዋታዎችን እያደረጉ ለዋናው ውድድር የሚበቁ ይሆናል።

የመጀመሪያው ቅድመ ማጣሪያ የሜዳ/ከሜዳ ውጪ ጨዋታዎች ከጷጉሜ 4-መስከረም 1/ መስከረም 6-8 ሲደረጉ ሁለተኛው የቅድመ ማጣሪያ የሜዳ/ከሜዳ ውጪ ጨዋታዎች ደግሞ መስከረም 27-29/ ጥቅምት 4-6 ድረስ እንደሚከናወን የወጣው መርሐ-ግብር ያስታውቃል። ከቻምፒየንስ ሊግ ሁለተኛው ቅድመ ማጣርያ የወደቁ ክለቦች ደግሞ በኮንፌዴሬሽን ካፕ ከጥቅምት 23-30 ተጨማሪ የማጣሪያ ጨዋታዎችን የሚያደርጉ ይሆናል። የተጠቀሱትን ዙሮች ያለፉ ክለቦች ከታህሣስ 23-ጥር 23 ድረስ ተጨማሪ የተጫዋቾች ምዝገባ አከናውነው የካቲት 3-5 የመጀመሪያ ጨዋታ ማድረግ ወደሚጀምረው ዋናው ውድድሩ እንደሚያመሩ ተመላክቷል።

ክለቦች በውድድሩ የሚጠቀሙባቸውን 40 ተጫዋቾች ማስመዝገብ ሲችሉ በተጠባባቂ ወንበር ላይ 9 ተጫዋቾችን አድርገው በጨዋታ 5 ተጫዋቾችን የመቀየር መብት እንዳላቸው ተጠቁሟል።




### ማስታወቂያ

ቶታልኢነርጂስ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንጋፋ ከሆኑትና በነዳጅ፣ በተፈጥሮ ጋዝ እና በዝቅተኛ ካርቦን ኤሌክትሪሲቲ ሽያጭ ላይ የተሰማራ ኩባንያ ሲሆን በዓለማችን በ130 አገራት ላይ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ቶታልኢነርጂስ በኢትዮጵያ ውስጥ እ.ኤ.አ ከ1950 ዓ.ም. ጀምሮና ከ16 ዓመት በፊትም ከሞቢል ኢጎት አፍሪካ ውህደት በጠቅላላው በመላው ሀገሪቱ ከ143 በላይ በሆኑ ነዳጅ ማደያዎችና 5 የነዳጅ ማከማቻ ዴፖዎች ሃላፊነት በተሞላው መንገድ የሽያጭ እና የአገልግሎት አሰጣጥን እያከናወነ ይገኛል:: በአንፃሩም ቶታልኢነርጂስ ማርኬቲንግ ኢትዮጵያ አ.ማ. በሀገሪቱ ካሉት የነዳጅ ኩባንያዎች መሪ ከሆኑት ከዘርፉ ኩባንያዎች በነዳጅና በዘይት ሽያጭ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በድሬዳዋ ከተማ የሚገኘውን የድሬዳዋ መጋላ ነዳጅ ማደያ ለግለሰብ ኦፕሬተር /የሽያጭ ወኪል/ መወዳድሮ በውል መስጠት ይፈልጋል፡፡

* ለመወዳደር የሚፈልጉ አመልካቾች ግለሰቦች፤

1. በትምህርት ደረጃቸው ቢያንስ 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቁና የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የነዳጅ ማደያው ሥራ የሚጠይቀውን የመሥሪያ ካፒታል /ገንዘብ/ በግላቸው የማቅረብ አቅም ያላቸው፣
3. ወቅታዊ የሆነና ያለፉትን 6 ወራት የሚያሳይ በባንክ የተረጋገጠ የባንክ ስቴትመንት ማቅረብ የሚችሉ ሆነው ከባንኩ የማረጋገጫ ደብዳቤ ማምጣት የሚችሉ፣
4. የነዳጅ ማደያውን የዕለት ተዕለት ሥራ በቂ ጊዜ ሰጥተው በግላቸው መምራት የሚችሉና፣ የሥራ ልምድ ማቅረብ የሚችሉ፣
5. አመልካቾች የድሬዳዋ ከተማ ወይንም አካባቢ ነዋሪ መሆን አለባቸው፡፡
6. ጊዜው ያላለፈበትና ተቀባይነት ያለው መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ማቅረብ የሚችሉ፣
7. የነዳጅ ማመላለሻ ቦቴ ያለው/ያላት ወይም ለመግዛት የሚችሉ፣

* ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ግለሰቦች፤

1. የማይመለስ ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ በመክፈል የማመልከቻ ሰነዱን ሙለጌ ህንፃ ሰባተኛ ፎቅ በሚገኘው ዋና መ/ቤታችን የሽያጭ ቢሮ ድረስ በመቅረብ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት መጀመሪያ ቀን ከሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 05 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 10:00 /አስር ሰዓት/ ድረስ የጨረታ ሰነዱን ገዝተውና ሞልተው መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ከላይ ከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ በኋላ የሚቀርብ የማመልከቻ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም::
3. ኩባንያው የተሻለ መንገድ ካገኘ ውድድሩን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ከማመልከቻ ሰነድዎ ጋር የሚከተሉት ደጋፊ መረጃዎች አባሪ መደረጋቸውን አይዘንጉ፤**

1. የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ፎቶ ኮፒ፣
2. ያለዎትን የገንዘብ አቅም ለማሳየት እንዲቻል ወቅታዊ የሆነ ቢያንስ የ6 ወር ተቀማጭ/ተንቀሳቃሽ ሂሳብዎን የሚገልጽ የባንክ ስቴትመንትና የባንክ የማረጋገጫ ደብዳቤ፣
3. የትምህርት ደረጃዎን የሚያሳይ የተሟላ የትምህርት መረጃ ፎቶ ኮፒ፣
4. ያለዎትን ንብረት የገንዘብ አቅም ለማሳየት እንዲቻል ወቅታዊ የሆነ የቋሚ የንብረት ባለቤትነት ማስረጃ ፎቶ ኮፒ /ካለ/፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ**

በስልክ ቁጥሮች - 011 465 11 25 / 011 465 45 25 ይጠይቁ::

**ቶታልኢነርጂስ ማርኬቲንግ ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር**

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1.የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ ኮልጌት ፓልሞሊቭ ካምፓኒ (COLGATE-PALMOLIVE COMPANY)

አድራሻ፡ 300 Park Avenue NEW YORK, NY 10022 United States of America

2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/3450/2014

3.የንግድ ምልክት፡-

4.ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ4/11/2007 ዓ.ም በVol-LXXIV No. 304 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው::

5.የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ10/06/2021 እስከ 10/06/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ሕግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-292 22/10/2014 (29/6/2022)

### አማራ ክልል

ለሜሮን ወንድወሰን በአፈ/ከሳሽ ኤፍሬም ሙላት እና በአፈ/ተከሳሽ ሜሮን ወንድወሰን መካከል ስላለው አፈ/ክስ ክርክር ጉዳይ አፈ/ተከሳሽ ፈጽመው እንዲቀርቡ ምክንያት ካላቸው ለሐምሌ 14 ቀን 2014 ዓ.ም 3፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ ቀን ይዘው እንዲቀርቡ በማለት ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአብክመ ጠ/ፍ/ቤት በደቡብ ወ/ዞን በደሴ ከተማ ወ/ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፀጋየ ገ/ሚካኤል መኮነን የተሽከርካሪው የሠሌዳ ቁጥር አ.ማ-03-21888 የተሽከርካሪው አይነት አውቶብስ ሞዴል KDN170L-CRMDYW የተሽከርካሪው የአገልግሎት አይነት ለሕዝብ ማመላለሻ የሞተር ቁጥር 2KD-1496309 የሻንሲ ቁጥር JTGSX23PX96065833 የተሽከርካሪው የመጫን አቅም 15 ሰው የአመታዊ ምርመራ ቀን 30/10/2013 ዓ.ም የሆነ ተሽከርካሪ ሠሌዳ የጠፋ ሲሆን ሠሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ፣ በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ይዞ እንዲቀርብ ይህ ካልሆነ ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የማዕከላዊ ጎንደር ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ**

ንብረትነቱ ሀዋ ደጀኔ ወኪል መህዲ ሰይድ ኮድ 3-21175 አ.ማ የሆነ ተሽከርካሪ የኋላ/የፊት ሠሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ ምትክ ሠሌዳ እንዲቀረጽላቸው በ 13/10/14 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀውናል፡፡ ስለሆነም ይህን ሠሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛውን ካላቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአብክመ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የሰ/ሸዋ ዞን መን/ትራ መምሪያ የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**